# የተቀደዱ የውኃ ጉድጓዶች

ጌታ ሆይ፡ አምናለሁ፡ ጌታ ሆይ፡ አምናለሁ
ሁሉም ነገር ይቻላል፡ ጌታ ሆይ፡ አምናለሁ።

ቆመን ለአፍታ አንገታችንን ደፍተን እንቆይ።

2 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ እናምናለን፡ ብለን እየዘመርን፡ በትህትና መንገዳችን፡ ለአንተ ለመግለጽ እየሞከርን ነው። ጌታ ሆይ፡ አሁን፡ የህይወትን እንጀራ፡ ለእኛ መቁረስህ እንድትቀጥል እንፀልያለን፡ ከቃልህ የምንፈልገውን፡ ሰጠን። በኢየሱስ ስም እንጠይቃለንና። ኣሜን።

3 ተቀመጡ። እኛ ሁላችንም፡ እኔን ጨምሮ፡ ሁሉን-ቻይ የሆነውን "አሜን" የሆነውን ቃል ብንናገር፡ የነሐሴው የእግዚአብሔር በረከቶች በዚህ ጉባኤ ላይ እንደሚወርዱ እርግጠኛ ነኝ።

4 ዛሬ ጠዋት ተቀምጬ አገልግሎቱን በጥንቃቄ እያዳመጥኩት ነበር፣ እያንዳንዱም ሰው ሃሳቡን የሚገልጽበት ልዩ ልዩ መንገዶች፡ ምስክርነቶች አስደስተውኛል። አዳዲስ እንግዶች ሲናገሩ መስማት፡ በተሳሳተ መንገድ ማሰቡ ይቅርታን ለመጠየቅ የመጣው የባፕቲስቱ ወንድማችንም። ስለዚህ አንድ ሰው—ትክክለኛ ሰው ሲሆን፡ አጥፍቻለሁ ብሎ ሲያስብ፡ ማለት—ጨዋ ሲሆን፡ በእውነት እጅግ አመሰግናለሁ። ይቅርታን የጠየቀው፡ ለእግዚአብሔር እንጂ፡ ለእኔ አይደለም። ስለዚህም—አመሰግናለሁ፡ ኢያችሁ። እግዚአብሔር ወንድማችንን እና ወንጌላዊው ወንድሙን ይባርካቸው።

5 አቤት፡ ያ ባፕቲስት'ማ፡ ታውቃላችሁ፡ እኔም ራሴ ባፕቲስት ቤተ ክርስትያን ነበርኩ። የሚሰዮናውያን ባፕቲስት ቤተክርስቲያን አባል ነበርኩ። በሰዎቹ መካከል ስትገኙ፡ ምን እንደሚሰማችሁ አውቃለሁ። እኔም የተሰማኝ፡ የማላውቀው—አይነት ስሜት ነው።

6 ለመጀመርያ ጊዜ የጴንጤቆስጤ እምነት ተከታዮችን የማየት አጋጣሚዬ አስታውሳለሁ፡ በዶዋጊያክ፡ ሚቺጋን ነበር… ይቅርታ፡ ዓሣ ለማጥመድ ወደ ዶዋጊያክ ሄጄ፡ ከዶዋጊያክ ወደ ኢንዲያና እየተመለስኩ፡ መንገድ ላይ ነበርኩ። እና "ኢየሱስ" የሚለውን ስም፡ በየመኪኖቹ ተጽፎ አየሁ፡ በዚያ ቀን አገልግሎታቸውን አደመጥኩ። በማግስቱ ወደ መድረክ እንድመጣና፣ ጥቂት ቃላትን እንድናገር ጠየቁኝ፡ ወጥቼ ተናገርሁ። እና አንተ… ከየትኛው ቤተ ክርስቲያን ነህ ብለው ጠየቁኝ፡ እኔም ባፕቲስት መሆኔን ነገርኳቸው።

7 በዚያ ምሽት አንድ ጥቁር ሽማግሌ ሰው ሊሰብክ ወጣ፡ ዕድሜው በሰማኒያዎቹ መጨረሻ ላይ ሊሆን ይችላል፡ እና ወደ መድረክ ወጣ። ሽማግሌው፡ ወደ መንገድ ሊያስቱት ጥቂት ነበር የቀራቸው። አገልጋዮች የሚለብሱት፡ ቬልቬት ኮላር፡ የተባለውን ለብሶ ነበር፡ በጎን በኩል ጸጉር መሳይ ትንሽ ነጭ ፈር ነበረው። እኔም አሰብኩ፦ "እነዚህ ሰዎች የሰነ መለኮት ምሁራኖች፡ ታላላቅ ሰዎች፡ እንዲህ አይነትን ሰው እንዴት መድረክ ይሰጣሉ? እንግዲህ፡ ይህ ሽማግሌ፡ አንድ ጥግ ወንበሩ ላይ ቁጭ ማለት ነበረበት።"

8 በዚያ ቀን ኢየሱስ በምድር ላይ ስላደረገው ነገር ይሰብኩ ነበር። እርሱ ግን፡ የሰብከቱ ርዕስ፡ ይመስለኛል፡ ከኢዮብ :7፣ 20፣ ነው እላለሁ፡ ቃሉ ያ እንደሆነ እርግጠኛ አይደለሁም። ሆኖም፡ ጥቅሱ ወይም የተወሰነው ክፍሉ፡ እንደሚከተለው ነው፦ "የአለምን መሰረት ስጥል አንተ የት ነበርክ፡ የንጋት ከዋክብት አብረው ሲዘምሩ፡ የእግዚአብሔርም ልጆች በደስታ እልል ሲሉ? " ሌሎቹ በምድር ስለሆነው ነገር ሲናገሩ ውለው ነበር፡ እርሱ ግን በሰማይ ስለተፈጸመ ነገር ተናገረ።

9 ከተናገረ፡ ከአምስት ደቂቃዎች በኋላ፡ የእግዚአብሔር መንፈስ፡ ነካው፡ ወለሉ ላይ በኃይል ዘለለና ተረከዞቹን ጠቅ ጠቅ አደረጋቸው። አቤት፡ የዚህን መድረክ ግማሽ የሚያክል፡ ሰፊ ቦታ ነበረውና፡ በፍጥነት እየተራመደ ሄዶ፡ እንዲህ አለ፦ "እኔ የምሰብክበት በቂ ቦታ የላችሁም።"

10 እንግዲህ ያኔ፡ የሃያ አመት ልጅ ነበርኩ። "ለዚያ—ለሽማግሌው ሰው እንዲህ ካሰደረገው፡ ለእኔ ምን ያደርገኝ ይሆን? " ብዬ አሰብኩ፤ አያችሁ?

11 ለአዳዲስ ወንድሞቻችን የኅብረታችን ሥርዓት መጠበቅ ተገቢ ነውና፡ በአግባብ እንደሚደረግ እንኳን ደህና መጣችሁ ማለት እንፈልጋለን። በጉባኤው ውስጥ፡ አንድ ካህን መኖሩን ሲናገሩ የሰማሁ መሰለኝ፡ በርግጥ፡ እኔ አይሪሽ ስለሆንኩ፡ ዘመዶቼ፡ ካቶሊክ ናቸው። ሌሎች ሁለትም፡ አንዱ ባፕቲስት እና ሌሎች ልዩ ልዩ ናቸው። ቀደም ሲል፡ ትንሽ ግራ ተጋብታችሁ ይሆናል። ከወንድሞች መካከል አንድ የጠቀሰልን ሰው የለም፡ እኔ ግን ለማረም እሞክራለሁ ብዬ አሰብሁ። ወንድም ሻካሪያን… ይህ ታላቅ ሰባኪ የጌታን መምጫ እጅግ እንደቀረበ በተረዳ ጊዜ፡ በታላቅ ደስታ ከተሞላ በኋላ፡ በማይታወቅ ቋንቋ—ለእኛ ተናገረን። የሚተረጉሙልን ሌሎች አስተርጓሚዎች አሉን። ቅዱስ ቃልም፡ እንደሚያዘው፦ "ተርጓሚ ከሌለ፡ ዝም ይበል ነውና።" ይሁን እንጂ—በልሳን የተነገረውን ከተረጎሙት፡ ትንቢት ይሆናል። ስለዚህ ሁለቱም በአንድ ጊዜ—ሲሆኑ ትንሽ ግራ ያጋባል። ይሔኛው፡ ያን ያህል ግራ የሚያጋባ አልነበረም፡ አያችሁ፡ ምክንያቱ፡ አንደኛው ትንቢት ሲናገር፡ ሌላኛው ግን ትርጉም ይናገር ነበርና። አያችሁ? ስለዚህ ያንን…

12 ወንድሞች እንዲረዱት ማድረግ አለብኝ ብዬ አሰብኩ፡ ከሁለቱ አንዳቸው'ኮ በትክክል እያሰተላለፉት ስለነበር፡ ወንድሞች ካልተረዱት… የሁለቱ የጊዜ አጠቃቀም አሰተውላችሁታል? የእግዚአብሄር መንፈስ በሱ አልፎ ትንቢት ሲናገር፡ ሌላኛው ትርጉም እያሰተላለፈ ነበር፡ ይተረጉመዋል፡ አንደኛው'ኮ ትርጉም እየሰጠ ነበር። ይህም ግልጽ ሊሆን ይገባል፡ አንዳንዴ፡ እናንተ'ኮ… እኛም ብንሆን… ስጋዊ አእምሮ የለንም… ልክ ዛሬ ጠዋት ይቅርታ እንደጠየቀ፡ ውድ ወንድማችን ነው። ለማይረዳው ሰው ትንሽ ግራ የሚያጋባ ነው። በዚያ ውስጥ ላሉ ግን፡ በውስጡ ላለን የትግሉ ዘማቾች ግን፡ እንደው፡ እነዚህ ነገሮች ምን እንደሆኑ፡ ይገባናል። ስለዚህ አስፈላጊ ከሆነ፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ትንሽ ነገር ለመናገር አሰቤ ነበር።

13 እንግዲህ፡ ይህ ስፍራ ይሄን የሚነገርበት እንዳልሆነ—አውቃለሁ። ይሁን እንጂ ሰው ሁሉ ትንንሽ ነገሮችን እየተናገረ ሰለቆየ፡ እኔም… ታውቃላችሁ፡ ያ ሽማግሌ፡ ጥቁሩ ሰውዬ "እኔ የምሰብክበት በቂ ቦታ የላችሁም፡" ብሏቸዋል።

ለእኔም እኔ የምሰበክበት **በቂ** ጊዜ የላችሁም እላችኋለሁ። [ጉባኤው ጭብጨባ እና ጩኸት አሰማ—አርታዒ።] ቶሎ አልጨርሰምና።

14 አንድ ሰው፡ አንድ ቀን እንዲህ አለ፦ "ለሃያ ዓመታት በቤተ ክርስቲያን ፓስተር ሆኖ የቆየ፡ አንድ አገልጋይ መጥቶ። ሁልጊዜ እሁድ ጠዋት በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ለሰላሳ ደቂቃ ያህል ብቻ ይሰብክ ነበር።" "ያን ቀን እሁድ ጠዋት ግን ሶስት ሰአት ሰበከ፡" አለ።

15 ከዛ የዲያቆናት ቦርድ ጠሩትና፡ "ፓስተር፡ በጣም እናመሰግናለን፡" አሉት። "ለመጽሐፍ ቅዱስ እና ለመብቶቹ እንደምትቆም—ሁሌም እናውቃለን፡" አሉት። እንዲህም፦ "በእግዚአብሔር ፊት ግልጽ እና ንጹሃን እንድንሆን ዘወትር ትመክረናለህ። በእውነት እናመሰግናለን፡ አንተ የእግዚአብሔር አገልጋይ እንደሆንክ እናምናለን። ስለ ዛሬ ጠዋት መልእክትም በእርግጠኝነት እናመሰግናለን። ግን፡" አሉት፡ "ልንጠይቅህ የምንፈልገው አንድ ነገር ብቻ ነው።" "እንደ ዲያቆን ቦርድ፡ የጊዜ ገደብ አርገንብሃል፡" አሉት። "ዘወትር እሁድ ሰላሳ ደቂቃ ብቻ ትወስዳለህ፡ ዛሬ ግን ሶስት ሰዓት ወሰደሃልና፡" አሉት። "እንግዲህ፡ እያንዳንዷን ነገር በምስጋና እንደተቀበልንህ፡ አስታውስ። በጣም ቆንጆ ነበር፡" አሉት። ታውቃላችሁ፡ ምቾት እንዲሰማው አደረጉት።

16 "እንግዲህ፡ ወንድሞቼ፡ ነገሩን ላጫውታችሁ፡" አላቸው። እንዲህ አለ፦ "ሁልጊዜ ጠዋት ሰወጣ... ወደ መድረክ በተጠራሁ ጊዜ፡" እንዲህ አለ፦ "እነዚህን ከረሜላዎች አፌ ውስጥ ከትቼ፡" "እነዚህን እየመጠትኩ እወጣለሁ፡" አላቸው። እንዲህ አለ፦ "ከረሜላው እንዲያልቅ ሰላሳ ደቂቃ ይፈጅበታል፡" አለ፡ "ከረሜላው ሲያልቅ፡" "ስብከቴን አቆማለሁ፡" አላቸው። እንዲህ አላቸው፦ "ታውቃላችሁ፡ ዛሬ ጠዋት ግን፡ ተጨማሪ ጊዜ እንደወሰድኩ አሰባለሁ። ከረሜላውን ተፍቼ፡ የልብስ ቁልፍ አፌ ውስጥ ከትቼ ነበር አላቸው።"

17 እኔ ግን ምንም ነገር አላስገባም፡ ኪሳችን ውስጥ የልብስ ቁልፎች እንደማይኖሩ ተስፋ እናደርጋለን። እንደው... መጥፎ ንግግር እንዳልሆነ ተስፋ አደርጋለሁ። እንደው... እግዚአብሔርም'ኮ ጨዋታ አዋቂ ነው፡ ታውቃላችሁ።

18 በዚህ ታላቅ እድል የህይወትን እንጀራ ቀላል በሆነ በራሴ መንገድ እንደገና ለመቍረስ፡ እ—እዚህ በመገኘታችን እና ይህን የሕብረት ጊዜ በማሳለፋችን፡ በጣም እናመሰግናለን። እንደው፡ ትናንት ማታ እዚህ እንደተናገረው ኢንግሊዛዊው ሰው፡ እንደ ቲኦሎጂ ሰዎች፡ እንደው፡ የሰባተኛ-ክፍል ትምህርት ይዤ፡ እሱን አይነት ሰው ጀርባ ላይ መነሳት አልወድም። እግዚአብሔር ግን የልቤን ሐሳብ እንዲተረጉምላችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። አያችሁ? ቃሎቼ ልክ ባይሆኑም'ኳ፡ ሐሳቦቼ፡ ልክ—እንደሆኑ ግን፡ እተማመናለሁ።

19 አሁን ከቅዱስ ቃል እናነባለን። ብዙዎቻችሁ አብራችሁ ማንበብ ትወዳላችሁ። ዛሬ ጥዋትም፡ ከነቢዩ፡ ከኤርምያስ መጽሃፍ ላይ፡ ረዘም ያለ ንባብ አነባለሁ፡ 2ኛው ምዕራፍ፡ እና ከቁጥር 1 እጀምራለሁ።

**የእግዚአብሔርም ቃል፡ ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፡**

**ሂድ በኢየሩሳሌም ጆሮ ጩኽ፡ እንዲህም በል፡ ጌታ እንዲህ ይላል፡ አስብኩሽ፡ የብላቴንነትሽን ምሕረት፡** እና የታጨሽበትንም

**ፍቅር፡ በምድረ በዳ** እና **ዘር ባልተዘራበት ምድር፡** እንደ **ተከተልሽኝ አስቤሻለሁ።**

**እስራኤል ለጌታ ቅዱስ ነበረ፡ የቡቃያውም በኩራት ነበረ፤ የበሉት...** እንደ **በደለኞች ይቈጠራሉ፡ ክፉም ነገር ያገኛቸዋል፡ ይላል ጌታ።**

**የያዕቆብ ቤት፡ የእስራኤልም ቤት ወገኖች ሁሉ ሆይ፡ የጌታን ቃል ስሙ፤**

**ጌታ እንዲህ ይላል፡ አባቶቻችሁ ከእኔ ዘንድ የራቁ፡ ከንቱነትንም የተከተሉ፡ ከንቱም የሆኑ፡ ምን ክፋት አግኝተውብኝ ነው?**

**እነርሱም፡ ከግብጽ ምድር** እና **ጉድጓድም ባለበት፡ የመራን ጌታ፡** በምድረ በዳም **በባድማ** ምድር **በውኃ ጥምና በሞት ጥላ ምድር፡ ማንም በማያልፍበትና፡ ማንም በማይቀመጥበት ምድር የመራን... ጌታ፡ ወዴት አለ አላሉም?**

**ፍሬዋንና በረከትዋንም ትበሉ ዘንድ፡ ወደ ፍሬያማ ምድር አገባኋችሁ፤ ነገር ግን** በገባችሁ **ጊዜ፡ ምድሬን፡ አረከሳችሁ፡ ርስቴንም እርኩሰት አደረጋችሁ።**

ካህናቱም፡ **ጌታ ወዴት አለ አላሉም? ባለ ኦሪቶችም አላወቁኝም፤ እረኞችም** ደግሞ **ዐመፁብኝ፡ ነቢያትም በበኣል ትንቢት ተናገሩ፥ የማይረባቸውም ነገር ተከተሉ።**

ስለዚህ **ከእናንተ... ጋር እከራከራለሁ፡ ይላል ጌታ፡ ከልጆቻችሁም ልጆች ጋር እከራከራለሁ።**

**ወደ ኪቲም** ምድር **እለፉና... ተመልከቱ፡** ወደ **ቄዳርም ላኩና፡ እጅግ መርምሩ፡ እንደዚህም ያለ ነገር ህኖ እንደ** ሆነ **እዩ።**

በውኑ **አማልክት ያልሆኑትን; አማልክቱን የለወጣቸው እንድ ሕዝብ... አለን? ነገር ግን ሕዝቤ ክብሩን ለማይረባ** ነገር **ለወጠ።**

**ሰማያት ሆይ፡ በዚህ፡ ተደነቁ፡ እጅግም** ደንግጡና **ተንጥቀጡ፡... ይላል ጌታ።**

**ሕዝቤ ሁለቱን ክፉ ነገሮች አድርገዋልና፤ እኔን የሕያውን ውኃ ምንጭ ትተውኛል፡ የተቀደዱትንም ጉድጓዶች፡ ውኃውን ይይዙ ዘንድ የማይችሉትን ጉድጓዶች፡** ለራሳቸው **ቆፍረዋል።**

20 በቃሉ ንባብ ላይ ጌታ በረከቱን ይጨምር። የጽሑፉ ርዕስ፡ **የተቀደዱ የውኃ ጉድጓዶች**—የሚል ሰያሜ መሰጠት፡ እፈልጋለሁ።

21 እዚህ ላይ፡ ቅዱስ ቃል ሲነበቡ፡ መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ፡ በምሪት የተሰጠ ነው። እኛም ወደ ጌታ ቤት የምንመጣው ለመታረም እና ለማስተዋል ነው። አንዳንድ ጊዜ... በመንገድ ላይ ጥቃቅን ነገሮች እናያለን።

22 ልክ እንደዚያ ወታደር፡ ቀድሞ ሲል፡ አንዳንድ ነገሮችን እየነገረን ነበር፡ ምናልባት ሌሎች አገሮች ለየት ያለ ሚሳኤል ሊኖራቸው ይችላል፡ እኛም—

ደግሞ በጦር ስልት ዙርያ፡ ያንን የሚመክት ነገር መፈለግ አለብን—የሚመስል ሐሳቦችን ተናግሯል።

23 እንግዲህ፡ በቤተ ክርስቲያንም፡ ሰው በሚሰብክበት መቅደስም ይሁን፡ ወይም በመስክ በወጣ በወንጌላዊም ተመሳሳይ ነው። የሆነ ነገር ሲጀማምር፡ አመጽ እየተነሳሳ፡ የልጅ ነገር የመሳሰሉ ነገሮች፡ ሲሰፋፉ ካየ፡ ያ ሰው፡ የእግዚአብሔር አገልጋይ ከሆነ፡ ያንን ነገር ከሰዎች አእምሮ እንዲርቅ መከልከል አለበት ይህም ሰዎቹ ከፋ እንዲርቁ ነው። እኛም እንደዚህ አይነት ቦታዎች ውስጥ እንድንገባ፡ ይህ እንዲሆን አንፈልግም።

24 እንግዲህ፡ የኤርምያስ ዘመን፡ ትንቢቱ፡ የኢሳይያስ—ኢሳያስ ከሞተ—ከሰልሳ ዓመታት በኋላ ነበር። ዋና ነብይ ሳይኖራቸው ሰልሳ አመት ገደማ ቆይቷል። ዕንባቆም እና አንዳንድ ትናንሽ ነቢያት ነበሩ፡ የመጨረሻው ዋና ነቢይ ግን ኢሳይያስ ነበረ። በዚያ ጊዜ፡ ህዝቡን ሀይ የሚላቸው፡ አልነበረም። መስመር ሰተው ነበርና። ሆኖም፡ አሁን በገቡበት—ሁኔታዎች ገብተው ብናያቸውም'ኳ፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነበሩ፡ ኤርምያስ ትንቢት ሊናገርላቸው መጣ። ኤርምያስም... ከግዞት በፊት ትንቢት ተናገራቸው፡ አብሮ በግዞት ተወሰደ።

25 እንዲሁም፡ ዳንኤልም፡ ከኤርምያስ በኋላ መጣ። ዳንኤል በዚያ ስለሚቆዩበት፡ ስለ ሰባው ዓመት፡ ከመጽሐፍ አስተዋልኩኝ አለ።

26 እንዲሁም፡ በመካከላቸው ሌላም ነብይ ነበር፡ ይህም ቀንበር ሰርቶ፡ ቀንበሩን በአንገቱ ላይ አሰረና፡ ይህ ቀላል ነገር እንደሆነና፡ በሁለት ዓመታት ውስጥ፡ እግዚአብሔር፡ መልሶ እንደሚያመጣቸው ተነበየ፡ ኤርምያስ ግን ከዚያ በበለጠ የሚያውቀው ነገር ነበረው። በስህተት ትንቢት የተናገረው ነቢይም፡ በዚያው ዓመት እንደሞተ እናውቃለን። እግዚአብሔርም እንዲቆም አልፈቀደለትምና።

27 በዚያን ዘመን የነበሩትን ሰዎች ሁኔታቸው አሁን አውቀናል። እንግዲህ እኔ—እዚህ ለምናገራቸው ጥቂት ቃላት፡ እና ማስታወሻዎች፡ በሌላ መንገድ እንድትረዱኝ አልፈልግም... ሌላ ዓላምም የለኝምና።

28 ድሮ ድሮ—ቃላቶች እና ማስታወሻ መያዝ የማያስፈልገኝ ዘመን ነበር። ሁለተኛው ሀያ-አምስት አመታት ካለፈኝ ጊዜ ወዲህ ግን፡ እንደ ድሮዬ—ማስታወስ አልችልም፡ ስለዚህ የተነሳሁበትን፡ አቅጣጫ ለማወቅ፡ ቅዱስ ቃላት ጽፌ እይዛለሁ። ለታመሙ እና በልዩ ልዩ ጉዳዮች ለመጸለይ፡ ረጅም ጊዜ ስለሚያስፈልገኝ፡ ወጥቼ ስለምሄድም፡ ማጥናት እንዳለብኝ ሆኜ ለማጥናት ጊዜ አይኖረኝም።

29 አሁን፡ የዚያ ዘመን ታላቅ ነቢይ፡ ነብይ ኤርምያስ ነበር፡ እርሱም አሞጽና ሌሎች ነቢያት በተነሱበት ዘመን የተነሣ ነበረ። አገሪቱ የገባችበት ገጽታ ባየ ጊዜ ተረበሸ። እና አንዳንድ ቦታዎች...

30 አንዳንዴ ስለ አገር ስትናገሩ፡ ስለ ተወሰኑ ቡድን—እንደሚያንጸባርቅ ሊመስል ይችላል። ያ አይደለም። የሀገሪቱ አጠቃላይ ገጽታን ነው። እኛም፡ ዛሬ፡ በ—በኤርምያስ ዘመን እንደነበረው ገጽታ፡ በእኛም ዛሬ በጣም ተመሳሳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡ ሕዝብ፡ እንደ ሕዝብ፡ ይብዛም ይነስ፡ ከእግዚአብሔር ርቀው፡ ወደ ጣዖት አምልኮ፡ የሚመስል፡ ሁኔታ ውስጥ፡ ገብተው ነበር። ይህም እንዲሆን

ያስቻለው፡ ከፑልቢቱ የሚነሳ ድካም ነው። ምክንያቱ፡ ፑልቢቱ በእግዚአብሔር ቃል፡ የጸና ቢሆን ኖሮ፡ እግዚአብሔር በመካከላችን እየሰራ እንዳለ፡ በሌሎች አብያተ ክርስትያናትም ይሰራ ነበር። እነርሱ ግን መስመር ሳቱ። እኔም ዛሬ ጠዋት—ስለዚህ ጉዳይ መናገር ፈልጌአለሁ። በእያንዳንዱ ዘመንም ይህ ፍጹም እውነት ሆኖ አግኝተነዋል።

31 ከጥቂት ጊዜ በፊት እንደጠቀስኩት፡ አሞጽ ይመስለኛል፡ "ነብይ፡ ወይም የነብይ ልጅ አይደለሁም" ያለው። ግን፡ አላቸው፦ "አንበሳ ሲያገሣ፡ የማይፈራ ማነው?

32 በምድረ በዳም የእውነት አንበሳ ሲያገሣ ብትሰሙት፡ እዚህ እናንተ በዙሪያችሁ በመካነ እንስሳት የምትሰሙት ሚያው ነው። በምድረ በዳ ሲጮህ ግን፡ ሁሉም መጠንቀቅ ይጀምራል አደን ለማደን፡ በየጫካው አድሬ አውቃለሁ። አንበሳ የአራዊት ሁሉ ንጉስ ነው፡ እና፡ ሲያገሳ፡ ጥንዚዛ ሳይቀር፡ ሌላው ሁሉ መጮህ ያቆማል። የ—ቀበሮዎች እና—ጅቦች ጭኸት፡ የሌሎች እንስሶች፡ የዝንጀሮዎች የጦጣዎች፡ የጥንዚዛዎችም፡ መንጫጫት ሁሉ፡ ማሰብያ ጊዜ ያሳጣችኋል፡ አንበሳ ከሩቅ ሲያገሳ ግን፡ ጥንዚዛ ሁሉ መንጫጫቱ ያቆማል። ሌሎች፡ ይፈሩታል። ሆኖም፡ እሱን ሊገድሉት የሚችሉ ብዙ ነገሮች አሉ፡ በአራዊት መካከል ግን ንጉስ እንደሆነ ይታወቃል።

33 እንዲህ አለ፦ አንበሳው ሲያገሣ፡ የማይፈራ ማን ነው? ጌታ እግዚአብሔር ተናገረ፡ ትንቢት የማይናገር ማን ነው? "

34 እና ያ ነው፡ እንደሚመስለኝ፡ ዛሬም ዘመኑ በዛ ተግዳሮት ተይዟል። እግዚአብሔርም ተናግሯል። አያችሁ? የግድግዳው የእጅ ጽሁፍ አይተናል፡ ስለዚህ በዘመን ፍጻሜ መሆናችንን ለማየት እና ለመተንበይ በጣም ቀላል ነው።

35 ከካቶሊካዊነት ጀምረን፡ በሁሉም የሐይማኖት ተቋሞች ክፍል፡ እግዚአብሔርን፡ እያየነው ነው፡ በሁሉም የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት፣ ቡድሃዎች፡ እና-ሌሎችም፣ ከህንድ፡ እና ከሌሎችም፡ ሕዝቡን እየጠራ፡ እየሰበሰበ ነውና። እኔም—ይህ ቀን መጥቶ በማየቴ፡ በጣም ደስተኛ ነኝ። እንግዲህ... ይህ—ዘመን ታላቅ ነው፡ ከታላላቆች በረከቶች መካከል አንዱ ነው።

36 እንግዲህ፡ ገና፡ ዓለም ሳይፈጠር በፊት፡ ነፍስ ሆነን፡ ብልቶቹ ሆነን ከእርሱ ጋር በነበርን ጊዜ፡ ገና ዓለም ሳይፈጠር በፊት ይሄን አውቄ ቢሆን ኖሮ። የዘላለም ህይወት፡ አንድ ብቻ ነውና፡ እሱም እግዚአብሔር ነው። እኛም ብልቶቹ ነን። ያኔ ዓለም ሳይፈጠር በፊት፡ ዕውቀት ኖሯቸው—የሚያስቡ አካሎች አልነበርንም፤ ነገር ግን ወደ ፊት የምንሆነው ሆነን፡ በአሳቡ ውስጥ እንኖር ነበርን። ልጁ አካሌ እንደሆነ፡ እኔም የአባቴ አካል እንደሆንኩ፡ እና ወዘተ፡ እኛም፡ የእርሱ አካል ነንና። በቀደመው እውቀቱ፡ የእግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ነን።

37 ያኔ ድሮ፡ አሁን እንዳወቅኩት ዓይነት እውቀት ቢኖረኝ፡ የጊዜን ሙላት የማየት አቅም ቢኖረኝ ኖሮ፡ እርሱም "ለምን ያህል ዘመን መኖር ትፈልጋለህ፡" ብሎ ቢጠይቀኝ? አሁን እኛ እስካለንበት ዘመን ድረስ፡ እስከ—ዓለም ታሪክ ፍጻሜ ዘመን ድረስ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ ለመትከል

የሚመጣበት ዘመን ድረስ ባልኩት ነበር። እንደ'ኔ ከዘመናት ሁሉ ይልቅ በጣም የከበረ ዘመን፡ አሁን ነው ብዬ አስባለሁ።

38 እዚህ ላይ እግዚአብሔር ነብዩን ሾሞ በላከው ጊዜ፡ እስራኤል በነቢይው እንደተከሰሰች እንገነዘባለን፡ በሁለት ታላላቅ ኃጢአቶች ተከሰሱ። አሁንም እነሱ ስላደረጉት ስለ ሁለቱ ነገሮች መነጋገር እንፈልጋለን። እናም፡ ከዚያ ተነስተን፡ ሰፋ ማለት እንፈልጋለን። እና፡ የሕያው ውኃ ምንጭ የሆነውን እግዚአብሔርን ረሱ፡ ለራሳቸውም ጉድጓዶችን ቆፈሩ። እግዚአብሔር ከሰጣቸው ነገር ተመለሱ፡ ራሳቸውም የሠሩትን ነገር በራሳቸው ቈፈሩ። ተከታተሉኝ፡ የውኃ ጉድጓዶቹም፡ ስለተሰበሩ፡ የሚያፈሱ ነበሩ።

39 እንግዲህ የተሰበረ ጉድጓድ ውኃን መያዝ አይችልም። ፈሶ ያልቃልና። እድገቴ በእርሻ አካባቢ ነውና፡ አሮጌ ጉድጓድ ምን እንደሆነና፡ ምን ያህል ያስቸግረን እንደነበረ አውቃለሁ።

40 እና ያ የሚያንጠባጥብ ጉድጓድ፡ የ—የዚህ ዘመን፡ ትክክለኛ ምሳሌ ይመስለኛል፡ ይህም ልንሰራቸው የምንፈልጋቸው ነገሮቻችን (ሁሉ) ሰውን አንድ ማድረግ፡ ህዝብ አንድ ማድረግ፡ ቸርቾችን አንድ ማድረግ፡ መቼም ቢሆን የአዕምሯዊ አድማስ ሙከራዎች ናቸው። ሜቶዲስቶችን ሁሉ ባፕቲስት የማድረግ ሙከራ፡ እና በተቃራኒው፡ እና የተለያዩ የሐይማኖት ተቋማት። ከመጀመርያም ያ፡ የእግዚአብሔር ፕሮግራም አልነበረም።

41 እግዚአብሔር አንድ መገናኛ ቦታ ብቻ አለው። በዘጸአት መጽሐፍ ውስጥ፡ “ስሜንም የማኖርባት ቦታ መርጫለሁ፡ ከህዝቡ ጋር የምገናኝበት ብቸኛው ቦታም ይህ ስፍራ ነው፡” ብሏል። ስሙን የሚያኖርበት ቦታ መርጧል። ስሙን በሚያኖርበት በዚያ ስፍራ፡ ከእስራኤል ጋር ይገናኛል። ዛሬ ከቤተክርስቲያኑ ጋር የሚገናኝበት ቦታ አለው፡ ስሙንም መረጠ፡ ስሙም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እና እውነተኛ አማኝ በኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን፡ በዚያ ይገናኘዋል። እግዚአብሔር ስሙን ለማስቀመጥ የመረጠው በዚያ ነው።

“የእግዚአብሔር ስም፡” ነው ያልከው?

42 እርሱ ራሱ “በአባቴ ስም መጥቻለሁ፡” ብሏል። ስለዚህ እግዚአብሔር ስሙን ያስቀመጠው፡ በክርስቶስ ነበር። በፈሰሰው ደም መገናኘት የምንችለው ሁላችንም በክርስቶስ ስንሆን ነው፡ በዚያም ትክክለኛ፡ እና እውነተኛ ህብረት ይኖረናል።

43 እግዚአብሔር፡ ሰውን በሚገናኝበት በኤደን ገነት ውስጥ፡ የመጀመሪያ ፕሮግራሙን አደረገ፡ ያ ግን በአዕምሯዊ ዕውቀት አልነበረም፡ ቢሆን ኖሮ፡ ሔዋን ከፕሮግራሙ አልተዛነፈችም ማለት ነው። የሰይጣን አእምሯዊ ፅንስ ሀሳብ እንደተቀበለች ግን እናውቃለን፡ “በእርግጥ፡ እግዚአብሔር አልወደደውም፡” እንደሚሆን ግን ተናግሯል! በዚህም የመቤዠት ቦታ መረጠ፡ ያም ደም እንጂ፡ የአእምሮ ፅንስ ሀሳብ አይደለም።

44 ስለዚህ እኛ አየር ጉስማ ላይ ነን፡ ሰዎች—ይህን ለማድረግ ሙከራ ማድረጋቸው—ሰዋዊ ተፈጥሮ ብቻ ነው። ጊዜ ቢኖረን፡ አድቅቄ አስቀምጠው ነበር፡ ይሁን እንጂ ያቺን ቁልፍ መጫን አልፈልግም። ስለዚህ በተቻለን መጠን ቀለል አድርገን “የሚያፈሱ ጉድጓዶች፡” ብለን እናልፈዋለን። እናም ይህ

ነገር እንደገና—በትክክል ተከሰቶ አይተነዋል፡ ከሙከራዎቻችን ሁሉ፡ አሁን እየኖርንበት ካለነውን ዘመን ትክክለኛ ሰዕላችን ነው።

45 የኢየሱስ ክርስቶስን ስም የሚጠራ፡ የትኛውም የእግዚአብሔር አገልጋይ ጥረት ከንቱ ነው ለማለት አይደለም። በአክብሮት እና በትህትና ሰሙን በመጥራቱ ብቻ ሊከበር ይገባዋል። በእነዚያ አድማስ ተሻግረው በወጡ ታላላቅ የወንጌል ሰርአቶች፡ እና የመሳሰሉት፡ በእነዚህ የመጨረሻ ቀናት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ሰር እስክናሰገባቸው ድረስ ሰዎችን አንድ ልብ ማድረግ አንችልም፡ ብዬ አሰባለሁ። ደህና የምንሆንበት ብቸኛው ቦታ እሱ ነው።

46 አንድ ሰው አንድ ጊዜ፡ ከሩቅ ከወደ ምስራቅ በኩል ደወለልኝና፡ እንዲህ አለኝ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ወደዚህ ወደ አሪዞና—መሄድክን ሰምቻለሁ፡ በዚያም ሄደህ—የደህንነት መንደር መሰርተዋል ሰማሁ።” ያ መልዕክት እንዴት እንደመጣ እናንተ ታውቃላችሁ፡ አላስካ ላይ የሚፈጸም ነገርና፡ ከዚያም አልፎ በካሊፎርኒያ የሚሆን ነገር ጌታ ነግሮኝ ነበርና፡ ነገሩ እንዲህ ነበር። እነሱ አሉ፦ “አሁን ያ እንዲህ የሚንቀጠቀጥ ከሆነ፡ ወዘተረፈ፡ የደህንነት ቀጠናው የት ነው? ”

47 እኔም አልኩኝ፦ “እኔ የማውቀው አንድ የደህንነት ቀጠና አለ። በክርስቶስ ነው። እኔ የማውቀው እሱ ብቻ ነው። በክርስቶስ ላሉት፡ ለእነርሱ... ”

48 እንግዲህ ኤርምያስም፡ “አልቃሻው ነብይ፡” ተብሎ ተጠርቷል። እናም እኔ፡ እንደማምነው፡ ይህን ነቢይ ያሰለቀሰው—ማለት፡ እንዲያነባ ያሰደረገው፡ እርሱ ነቢይ ሰለሆነ (የጌታም ቃል እንዲህ ሲሆን በማየቱ ነው) ሕዝቡም ወጋቸውን ተከትለው በመሄዳቸው፡ ደህንነት ያገኙ መሰሎአቸው በማየቱ፡ እናም የሚመለሱበት ምንም መንገድ ባለመኖሩ ነው።

49 በቀጥታ፡ ወደ ግዞት ይሄዱ ነበርና፡ ምክንያቱ ማንም ሁን ምንም ሁን፡ የዘራኸውን እንደምታጭድ እናውቃለንና። እኛም እንደ ሀገር፡ አጭደናል፡ ማለቴ፡ ዘርተናል፡ ደግሞም እናጭዳታለን። ጌታ ቢፈቅድ፡ ነገ ከሰዓት ላይ፡ ሰለ **ምጥ ህመም፡** እናገራለሁ፤ እና እኔ—ያለ ምንም ነገር ማለፍ የማንችል መሆናችን፡ ነክቼ አልፋለሁ። የዘራነውን ማጨዳችን ግዴታ ነው።

50 እግዚአብሔር ዛሬ የሠራነውን የተበላሸ ክርሰትና እያየ፡ ህዝቡንም ክርሰትና-መሳይ ወደ ሆነ ነገር እንዳጣመምነው እያየ፡ እኛን ዝም ብሎ ካለፈን፡ ብሎ ወንድም ሙር ተናግሯል፦ “ሰዶምንና ገሞራን የማስነሳት እና፡ ሰላቃጠላቸው ይቅርታ የመጠየቅ ግዴታ አለበት ብሏል።” ትክክል ነው፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር አሁንም ጻድቅ ነው። እና ኢፍትሃዊነት በነገሠበት ሁሉ፡ ሰዎች የሚዘሩትን እንዲያጭዱ የሚያደርጋቸው ወደ ቅድሰናውና ወደ ቃሉ እየደረሰ—ነው፡ እኛም ይህን ማድረግ አለብን።

51 አሁን የሕይወት ውኃ ምንጭ፡ የሆነውን እርሱን ትተው፡ ጉድጓድን ቈፈሩ።

52 አሁን እዚህ ጉድጓድ ምን እንደሆነ የማያውቅ ሰው ሊኖር ይችላል። የውኃ ጉድጓድ የምንጭ ውኃ የሚተካ ሰው-ሰራሽ ጉድጓድ ነው። ሰው የቆፈረው ነገር ነው። ጉድጓድ የምታውቁ ሰንቶች ናችሁ? እሺ። በጣም ጥሩ፡ ዛሬ ማለዳ ብዙ የገጠር ተወላጆች እዚህ አሉ። እነሱም... ድሮ በዚያ የነበረውን ያ ያረጀ የውኃ ጉድጓድ ትዝ ይለኛል፡ ሁልጊዜም ከዚያ ለመጠጣት እፈራ ነበር። ሰው-ሰራሽ፡

ማጠራቀሚያ—ነበር። እና ፈጽማችሁ አታምኑትም። ጉድጓድ ላይ መታመን አትችሉም።

53 ሰው ሰራሽ የሆነ ማንኛውም ነገር ብዙውን ጊዜ ጥሩ አይደለም። ልክ ጊዜን ወደ—ወደ—ዑደቱ ውስጥ እንዲገባ ያደረገ ጌታ—ምድርም እንድትዞር ያደረጋት፡ ዘመን በተሻገረ ቁጥር፡ በየአመቱ፡ በየቀኑ፡ በየሰዓቱ፡ ፀሐይ ስትጠልቅ፡ በጭራሽ አይቆምም። ነገር ግን አሉ የተባሉ በጣም ጥሩ ሰዓቶች፡ በወር ውስጥ ብዙ ደቂቃዎች እንደሚበላሹ፡ ጥርጥር የለውም። አያችሁ፡ እግዚአብሔር የሚያደርገው ነገር ሁሉ ግን፡ ፍጹም ነው፡ ሰው የሚያደርገው ነገር ፍጽምና ይጎድለዋል። እንግዲያውስ ፍፁም የሆነውን መያዝ ስትችሉ፡ ሰው የሰራውን ለምን ትቀበላላችሁ?

54 ስለ እኛ ስለ ጴንጤቆስጤ ሰዎች ደጋግሜ ተናግሬአለሁ። አያችሁ፡ በርግጥ፡ እንደምናውቀው፡ ከእግዚአብሔር ከአካሄድ፡ የወጣን ሰዎች አይደለንም—አይደለንም፤ ይሁን እንጂ በመካከላችን ሌላውን ለመምሰል የሚሞክሩ ሰዎች እንዳሉን እናውቃለን። ይህም ስጋዊነት ነው። ይህን ለማድረግ ይሞክራሉና። በመጽሐፍ ቅዱሰም ተደርጓል፡ "አንዱ፡ 'እኔ የጳውሎስ ነኝ፡' 'እኔም የሲላስ ነኝ፡" ወዘተረፈ። እነዚህ ግን—ሌላ ሰው ያደረገውን ወይም እያደረገ ያለውን ለማስመሰል የሚሞክሩ ናቸው።

55 ስማያት በእውነተኛው ነገር ተሞልቶ ባለ ጊዜ፡ የውሸት ማስመሰልን መቀበል ለምን አስፈለጋችሁ፡ "የተሰፋው ቃል ለእናንተ እና ለልጆቻችሁ ነው" ተብሎ ሳለ? የተለየ ነገር ለምን እንቀበላለን? መጽሐፍ ቅዱስ ያልተበረዘ የእግዚአብሔር ቃል ሆኖ ሳለ፡ የሐይማኖት አዋልድ ወይም ዶግማ ለምን እንይዛለን? ለመጨመር ወይም ለመቀነስ ለምን እንሞክራለን፡ ጌታ ኢየሱስ በራዕይ 22፡18 ላይ "ማንም ከእርሱ አንዲት ቃል የቀነሰ፡ ወይም በእርሱ ላይ አንዲት ቃል የጨመረ፡ ዕድሉ ከሕይወት መጽሐፍ ይወሰድበታል" እየተባለ?

56 እግዚአብሔር የሰውን ዘር መጀመሪያ ባደረገ ጊዜ... በምድር ላይ፡ በቃሉ እንደሚኖሩ ነግሯቸዋል። አሁን የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሰንሰለት ነው፡ እናንተም ከርሱ ጋር በሲኦል ዙርያ ታልፋላችሁ፡ የሰንሰለቱ ጥንካሬም ደካማ በሆነው አገናኙ ላይ ብቻ ነው፡ እግዚአብሔርም እያንዳንዱን ቃል እንድንጠብቅ ይፈልጋል። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያው ነገር ነበር፡ አንድ ቃል ብቻ በመሰበር የሰውን ልጅ በሞት ጨለማ ውስጥ ገባ።

57 ኢየሱስ በመጽሐፍ ቅዱስ መካከል መጥቶ፡ እንዲህ አለ፡- "ሰው በቃል ሁሉ እንጂ፡ በእንጀራ ብቻ አይኖርም።" ከቃላቱ ክፍል ብቻ ሳይሆን፡ ወይም ዘጠና ዘጠኝ ከመቶ፡ ልክ እንደ ሔዋንና አዳም፡ በቃል ሁሉ።

58 በመጨረሻው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ደግሞ ራዕይ 22፡18፣ እንዲህም አለ፡- "ማንም ከዚህ ቃል የቀነሰ ወይም በእርሱ ላይ አንዲት ቃል የጨመረ!"

59 ታዲያ ይህ የእግዚአብሔር የራሱ ሃሳብ ሆኖ ሳለ፡ የአንድን ሰው ሃሳቦች እዚህ ውስጥ ማስገባት ለምን ያስፈልገናል? -የተናገረውን ልንወስድ ያስፈልጋል። ደግሞም እንዲህ ተብሎ ተጽፏል፡- "የሰው ሁሉ ቃል ውሸት ይሁን፡ የኔም እውነት ይሁን።"

60 የዚህ ነቢይ ጉዳይ የነበረው ይሄ ነው። በኤርምያስ ዘመን፡ እርሱ ነቢይ ነበርና፡ የእግዚአብሔር ቃል ነበረው። ሌላኛው ሰውዬ ግን እንግዳ ነገር

ሊቀላቅል ሞከረ። ነገርዬው፡ የምትደገፉበት ነገር አይደለም። እነዚህ ታንከሮች ለመጠቀም ከምንሞክራቸው ስርዓቶች ጋር፣ ኦሪጂናሉ የእግዚአብሄር ቃል ስፍራ ለመተካት ከሚፈልጉ ጋር አመሳስላቸዋለሁ።

61 ስፍራውን ሊተካ የሚችል፡ የለምና። እግዚአብሔር ነውና። "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ቃል ስጋ ሆነ በእኛም መካከል አደረ።" ዕብራውያን 13፡8 እንዲህ ይላል፦ "እርሱ ትናንትና፣ ዛሬም፣ ለዘላለምም ያው ነው።" ከዚህ መራቅ እንዴት እንችላለን? እውነት መሆኑ ግድ ነው። ያው ሆኖ ይኖራልና። በእያንዳንዱ መርህ ሁሉ ያው ነውና።

62 እናንተ ባፕቲስቶች እና ሜቶዲስቶች፡ የምትደስቱበት ምክንያት ይህ ነው፡ ካቶሊክ እና ፕሪስባይቴሪያኖች፡ ሌሎችም፡ በመገኘቱ ይደስታሉ። በሆነ ስፍራ፡ በውስጣችሁ፡ እግዚአብሔርን ተቀብላችኋልና። ምናልባት አንዳንድ ጊዜ በአእምሮአዊ መንገድ፡ ምናልባት የእግዚአብሔር ኃይል ተሰምቶህ ሊሆን ይችላል፡ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነህና፤ ነገር ግን በእውነት ወደ እግዚአብሔር ስትመጡ፡ እንደ እግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች፡ በርሱ ዘንድ ያላችሁን ስፋራ ስታውቁት፡ እግዚአብሔር እንዲኖራችሁ የፈለገው፡ ያን ታላቁን ደስታ የሚያመጣው ያ ነው።

63 አሁን ደግሞ በቅዱስ ማርቆስ ምዕራፍ 16 ላይ ኢየሱስ እንዲህ ሲል እንዳልተናገረ እናስተውላለን፡ "ሂዱ ወንጌልን ስበኩ፡" አለ እንጂ። "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ እና—እና—እና አስተምሩ" አላለም። የመንፈስ ቅዱስን ኃይል እያሳያችሁ፡ ወንጌልን ስበኩ፡ ነው! "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱና፡ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል አሳዩ።"

64 ከስፖንሰሮች፡ አንዱ ከሆነው ወንድም ጋር ስንነጋገር… በህንድ፡ ቦምቤይ በነበረኝ ሰብሰባ፡ እንዲሁም በደቡብ አፍሪካ እና በተለያዩ ስፍራዎች፡ ሚስዮናውያኖች እንደ ቃል ወይም እንደ ምሁራዊ ፅንሰ ሀሳብ አርገው አሰበውት ነበር። ነገር ግን አንድ ቀን በሰብሰባ ላይ፡ መንፈስ ቅዱስ ራሱ፡ በወረደ ጊዜ፡ በአንድ መሠዊያ ጥሪ ብቻ፡ በዚያው በቆሙበት መሬት ላይ፡ ሠላሳ ሺህ የአገሩ ተወላጆች አዳነ። እዚያ የቆሙ ሴቶችም፡ ወደ ዓለም ሲመጡ እንደነበረ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ራቁታቸውን ሆነው ነበር፡ ክርስቶስን ለመቀበል እጃቸውን ባነሱበት ቅጽበት ግን…

65 መንፈስ ቅዱስም በዚያ ስፍራ ወርዶ በአንድ ጊዜ ሃያ-አምስት ሺህ ሰዎችን፡ ከዊልቸሮች፡ እና ከአልጋዎች እና ስትሬቸሮች ፈወሰ። በማግሥቱ፡ የከተማው ከንቲባ፡ በመንገድ ላይ የሚወርዱትን እነዚህን የጭነት መኪናዎች አይቶ ጥሪ አደረገልኝ።

66 እነዚያ ሴቶች፡ እራቁት መሆናቸውን ሳያውቁ፡ ራቁታቸውን ቆመው ነበር። መንፈስ ቅዱስ በወረደባቸው ጊዜ ግን፡ ከሰዎች ፊት ለመራቅ እጃቸውን አጣጥፈው ይሄዱ ነበር።

67 አሁን እያስገረመኝ ያለው ነገር እኛ አሜሪካ ውስጥ እራሳችንን የክርስቲያን ህዝብ ነን እንላለን፡ በእግዚአብሔር ፊት ግን፡ ከአመት ወደ አመት፡ ሴቶቻችን፡ እራቁት እየሆኑ ሄዱ። ይሁን እንጂ የበለጠ መልበስ ነበረባችሁ። ክርስቶስን አብዝታችሁ በለበሳችሁት ቁጥር፡ ስለ ሁኔታዎቻችሁ የበለጠ እንድታውቁ

ያደርጋችኋልና። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች በጎዳና ላይ የሚያደርጉትን እርምጃ እታዘባለሁ፣ በአእምሯዊ እይታ ትክክል ነው ወይ እላለሁ። ያንን ሲያደርጉ ነገሩን ያልተገነዘቡት ይመስላል፡ እያደረጉ ያሉት ነገር፡ ራሳቸውን ለዲያብሎስ ማጥመጃ እያደረጉ ነው፡ ነፍሳትን ወደ ገሃነም እየላኩ ነው። ትክክል። ዓለም ግን በኤርምያስ ዘመን እንደነበረው አሁንም በመበስበስ ውስጥ ነች።

68 ወደ ውኃው ጉድጓድ እንመለስ። እንግዲህ፡ ጉድጓድ በራሱ የሚሞላ ስላልሆነ አትተማመኑበትም። ለመሙላት ወቅታዊው ዝናብ መጠበቅ ያስፈልጋችኋል፡ ወቅታዊ ዝናብ ማለት ወቅታዊ ሪቫይቫል፡ እሱን ለሞሙላት፡ ትንሽ ሪቫይቫል **በዚህ**፡ ትንሽ ሪቫይቫል **በዚያ** ይደረጋሉ። ስለዚህ ሊታመን አይችልም። እራሱን መሙላት አይችልም። ለራሱ፡ ጎዶሎ ነው። ይሄን ማድረግ አይችልም። ለመሙላት፡ ዝናብን የሚጠብቅ ነው።

69 ጉዱጓዱ፡ ዝናብ ከየት—እንደሚያገኝ፡ ውኃው ከየት እንደሚመጣለት፡ አሁን እናስተውል። አቧራው ሁሉ ከሚጠራቀምበት ከቆሸሸ ጉሮኖ፡ ከቆርቆሮ ጫፍ ላይ፡ ይመጣል፡ ቀጥታ ዝናቡ ያጥበዋል፡ ሰው-ሰራሽ ወደ ሆነው ጉድጓድ፡ ወደ ጉድጓድ ይወርዳል። ልክ እንደ ገንዳ ይሆናል። ከጉሮኖ ላይ የተጠራቀመውን፡ የእንስሶች እና የጋጣውን ሽታ ሁሉ፡ ወዘተረፈ፡ አጥቦ ያወርድና ይከማቻል። ማለት ንፋሱ—በጉሮኖው ዙርያ ያሉትን ውዳቂ ነገሮች ያነሳቸውና፡ ዝናቡ፡ ወቅታዊው ዝናብ መጥቶ፡ ወድያው ያጥበዋል።

70 ከዚያም ውኃው በሰው-ሰራሽ መተላለፍያ በሰው-ሰራሽ አሸንዳ፡ ወደ ሰው-ሰራሽ ማጠራቀሚያ እንዲገባ ይደረጋል። እና እዚያ ሲደርስ፡ ቆሻሻ ነው፡ እጅግ ቆሻሻ ስለሆነ በላዩ ላይ ማጣሪያ ጨርቅ ታደርጋላችሁ፡ ወይም መጠጣት አትችሉም። እንግዲህ፡ ልብ በሉ፡ ሰው-ሰራሽ በሆነ መተላለፍያ፡ ሰው-ሰራሽ በሆነ አሸንዳ፡ ከጣራ ወደ ገንዳ የወረደ ነው። ከዚያ አንዳንድ ነገሮች እና ነፍሳት ለመከላከል፡ ከላዩ ላይ ሰው-ሰራሽ የሆነ ወንፊት ይደረግበታል።

71 አሁን፡ በእነዚያ ቀናት፡ ውኃው ወደ ሰው-ሰራሽ የእምነት ተቋማት-... ፡ ወይም፡ ገንዳ ውስጥ ከገባ፡ ከጥቂት ቀናት በኋላ፡ አንድ ነገር እናስተውላለን። ይቅርታ። ይቅርታ። በጣም ጥሩ። እንግዲህ ከሁሉም አይነት የሰነ መለኮት ነገሮች፡ አጣጥቦ ካወረደበት—በኋላ፡ አሁን አንድ ነገር እንረዳለን፡ ጥቂት ቀናት በዚያ ከቆየ በኋላ፡ የማይንቀሳቀስ ይሆናል።

72 በቤተ ክርስቲያን ታሪክም፡ ሁሉም ሰው ያውቃል፡ እግዚአብሔር የሆነ ነገር፡ መልዕክት በላከ ጊዜ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ የወረደ ትኩስ ይሆናል፡ በኋላ—መሰራቹ ከሞተ በኋላ (ወይም ማንም ይሁን፡ ተሐድሶ አራማጅ፡ ወይም የፈለጋችሁትን ብላችሁ ጥሩት)፡ ከእርሱ ሞት በኋላ፡ ስርዓት በማቀናጀት ተቋም ይመሰርታሉ። ተቋም በመሰረቱበት ቅጽበት፡ ወዲያው በዚያ ይሞታሉ። ዳግም አይነሳም። በእያንዳንዱ ዘመን ሆኗል፡ ኋላ፡ ከቱንቢው በኋላ።

73 እዚህ የተቀመጠው እኚህ የካቶሊክ ቄስ ለማክበር፡ እግዚአብሔር ቤተ ክርስትያንን ሲያደራጃት... ወይም፡ ማደራጀት ማለቴ አይደለም፡ እግዚአብሔር ቤተ ክርስትያንን አደራጅቶ አያውቅምና። በዚህ ዓይነት ንግድ ውስጥ አይገኝም። ልጆች በመውለድ እንጂ፡ ድርጅት ላይ አይደለም። ስለዚህ፡ እግዚአብሔር በበዓለ ሃምሳ ቤተክርስቲያንን ሲጀምራት። በመጨረሻ በኒቂያ፡ በሮም፡ አደራጁአት፡ እናም ኃይሏን ያጣችበት በዚያ ነው።

74 ከዚያም በኋላ ወደ ሉተራን ተሐድሶ እንደርሳለን፡ ያም ታላቅ ነገር ነበር። “ጻድቅ በእምነት ይኖራል፡” የሚል የእግዚአብሔር ቃል ተሰጠ። ይህ በሆነ ጊዜ፡ ሁሉም በአንድነት፡ አንድ ሆነው ከመዝመት ይልቅ፡ ከመነሳት ይልቅ፡ ራሳቸውን ከዚህ ቡድን በመለየት፡ የሉተራን ቤተ ክርስቲያን አደራጁ፡ ከዚያም ሞተች።

75 ከሱ በኋላ እግዚአብሔር፡ ሁለተኛው የጸጋ ስራ መልዕክት የነበረው፡ ጆን ዌስሊን አስነሣ፡ ያም ድንቅ ነበር። ከዌስሊ እና ከአስበሪ በኋላ ግን፡ አደራጅዋት፡ ሞተች።

76 ከዛ ብኋላም ስጦታዎቹ የተቃኙበት ጴንጤቆስጤዎች መጡ። ጥሩ እየሰሩ ቆዩ፡ ታዲያ ምን ተፈጠረ? ድርጅት አደረጓት እና ሞተች። በትክክል።

77 እንግዲህ በዚህ ሁሉ መካከል ግን፡ እግዚአብሔር ከትውልድ ሁሉ ቅሬታዎችን እየጠራ ነበር። አዎን ይጠራ ነበር። ለእኛም የመውጣታችን፡ የመሰብሰባችን ዘመን ይህ ነው። እኔም እንደማስበው፡ ፉል ጎስፐል ቢዝነስ ሜን ግድግዳዎችን በማፈራረስ ረገድ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል እላለሁ፡ እንዲህ በማለታቸው፡- “በመካከላችን ልዩነት የለም። በድርጅት ሳይሆን በአንድ መርህ፡ አንድ ላይ ተሰባሰበን እግዚአብሔርን እናምልክ አሉ።” ድርጅት ቢሆን ኖሮ፡ አሁን ከዚህ መድረክ እወርድ ነበር። ምንም ግንኙነት የለኝምና።

78 ታዲያ ምን ይሁን ህብረት ሊሆን ይገባዋል፡ በትንሳኤው ኃይል፡ በክርስቶስ ዘንድ የሚሆን ህብረት እንጂ፡ የሐይማኖት ስርዓት ህብረት መሆን የለበት። ህይወትንና፡ መወለድን የሚያመጣው ይህ ነው።

79 ከልደት በፊት፡ ልደት ከመሆኑ በፊት ሞት መኖሩን እንገነዘባለን። መወለድ ምስቅልቅል ነው፡ የማንም አወላለድ ይሁን ግድ የለኝም። የአሳማ በረት ይሁን፡ ወይም—የትም ይሁን፡ ምሰቅልቅል ነው። አዲሱ ልደትም እንዲሁ ነው፡ አደርገዋለሁ ብላችሁ የማታስቡትን ነገር እንድታደርጉት ያደርጋችኋል። ለራስህ ልትሞት ስትዘጋጅ ግን፡ በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት ሆነህ፡ ዳግመኛ ትወለዳለህ፡ ከዚያ ነገሮች ይከፈታሉ፡ ህይወት አዲስ እይታ ትሆንልሃለች፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት እንጂ፡ ጥቂት ንድፈ አሳብ ወይም የሐይማኖት ስርዓት አልተቀበላችሁምና።

80 ወይም፡ በጽሑፍ ያለውን ቃል እንኳን፡ በመንፈስ ቅዱስ ሕያው መሆን አለበት። የቱንም ያህል ሥነ መለኮት ቢኖራችሁ፡ የሞተ ነው። ህይወት ወደሚያገኛበት ሂደት እስኪደርስ ድረስ፡ እፍኝ ያህል ስንዴ ልይዝ እችላለሁ፡ ስንዴው ግን ፈጽሞ ህይወት የለውም። እናንተም የፈለጋችሁትን ያህል የዶክትሬት ዲግሪ፡ ፒኤች፣ ኤልኤል፣ ሊኖራችሁ ይችላል፤ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖራችሁ የግል ልምምድ፡ መንፈስ ቅዱስ በላያችሁ መጥቶ ሕያው እስከሚያደርግላችሁ ድረስ፡ ስለዚህ ስንዴው አይጠቅምም። መማራችሁ በከንቱ ነው።

81 ባለፈው ማታ እንግሊዛዊ ሰው በተናገረው ነገር፡ እጅግ ተገርሜ ነበር። የነበረው ትምህርት ሁሉ፡ እንደ ጳውሎስ፡ ክርስቶስን ለማግኘት፡ የሚያውቀውን ሁሉ መርሳት ነበረበት፡ አላደርጋቸውም ብሎ ያሰባቸውን ነገሮች አደረገ።

82 እግዚአብሔር የሚያደርገው ግን በዚህ መንገድ ነው፡ በትምህርት ስርዓታችን ውስጥ ያዋርደናል። ድንቁርናን መደገፌ ሳይሆን፡ ልዩነቱን ልነግራችሁ እየሞከርኩ ነው። ትምህርት ሕይወትን በፍጹም አያመጣም።

ህይወት ለማምጣት የእግዚአብሔር መንፈስ ይጠይቃል፡ ህይወትም ከአእምሯዊ መነቃቃት መምጣት የለበትም። ከመጽሐፍ ቅዱስ፡ ከቃል ሪቫይቫል መውጣት አለበት፡ ያ ቃልም ትናንትና፡ ዛሬ፡ እና ለዘላለም ያው ነው። ዛሬ ሲወርድ፡ እና ህይወት ሲሰጥ፡ በሐዋርያት ስራ 2 ላይ የነበረው ተመሳሳይ ውጤት ያፈራል። በትክክል። ድባቡን የሚያስተካክለው የእግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ፡ ሁል ጊዜ አለ፡ ሁልጊዜም ይኖራል።

83 ነገሮችን ለመስራት ድባብ ያስፈልጋል። ለዛ ነው ወንዶች ሁል ጊዜ የምትማሩት "ልጆቻችሁም ወደዚህ የምታመጡት።" አዎን፡ በትክክል እውነት ነው። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት፡ ልጄ፡ ርብቃ፡ ገብታ ተቀምጣ በማየቴ ደስ ብሎኛል። እንዳንዶቻችሁ ሴትዋ ላይ አይኔ ሰጠቅስ ያያችሁኝ፡ ልጄ ናት፡ መጥታ ቁጭ እንድትል ነው። የመንፈስን ጥምቀት እንድትቀበል እፈልጋለሁ፡ ለዛ ነው እዚህ በስብሰባ ላይ ያለችው። ዓላማው ያ ነው። ድባብ ይጠይቃል።

84 ድሮ ዶክተር ቦሰዋርዝ "የዶሮ እንቁላል ወስደህ በፓፕ በታች ብታስቀምጠው፡ ጫጩት ይፈለፈላል፡" ይል ነበር። ለምን? እንቁላል ስለሆነ ትክክለኛ ድባብ ሰላገኘ።

85 ሜቶዲስት ብትሆን፡ ባፕቲስት፡ ፕሪስባይቴሪያን፡ ግድ የለኝም፡ በትክክለኛ ድባብ ውስጥ፡ አዲስ የተፈለፈለ የእግዚአብሔር ልጅ ይወለዳል። ምንም አይነት የሐይማኖት ተቋም ታግ ይኑራችሁ፡ ይሄን የሚያደርገው ድባቡ ነው።

86 ከብት እርባታ ውስጥ እሰራ ነበር። ወደ ጫካው ስናወጣቸው ጠባቂውን እየዋለሁ፡ ከሚበሉበት አውጥተን—ከማሳው አውጥተን፡ ወደ ጫካው እንወስዳቸው ነበር። በበሩ አጠገብ ይቆምና፡ በተንሸራታች አጥር ውስጥ አልፎ ይመለከታቸዋል። በፍጹም ብራንዶቻቸው ልብ ብሎ አያውቅም፡ ምክንያቱ በዚያ የሚያልፉት ብዙ ዓይነት ብራንዶች ስለሆኑ። ነገር ግን የሚያተኩረው አንድ ነገር ላይ ነበረ፡ የደም ታግ ላይ። ትሩብሬድ ሄሬፎርድ ዝርያ ካልሆነ በቀር በዚያ ጫካ ማለፍ አይችልም፡ ያንን ጫካ የሄሬፎርድ ማህበር ማስማርያ ነውና። እርባታውን መብት በትክክል ለመጠበቅ፡ የደም መለያ ሊኖረው ይገባል።

87 በፍርድ ቀንም እንደዚያ ይሆናል ብዬ አስባለሁ። ሜቶዲስት፣ ባፕቲስት፣ ጴንጤቆስጤ ወይም ፕሪስባይቴሪያን ነህን ወይ ብሎ አይጠይቀኝም፡ ነገር ግን የደም መለያውን ያያል። "ደሙን ባየሁ ጊዜ አልፋችኋለሁ።" ነገሩ ያ ነው።

88 ስለዚህ እነዚህ የውኃ ጉድጓዶች፡ ጥቂት ጊዜ ከተቀመጡ በኋላ፡ ድባባቸው… የማይንቀሳቀሱ ጥቅም አልባ ይሆናሉ። እናም ያኔ፡ ደግሞ፡ የእንቁራሪቶች የእንሽላሊቶች የእባቦች የነፍሳት እና የጀርሞች፡ የሌሎችም-መኖሪያ ይሆናል፡ ምክንያቱም ወደ ውስጥ የገባው ነገር የቆመ ድባብ ነው። በጋጣ ጣሪያ ላይ፡ ወይም በጋጣው አቅራቢያ ካለ ቤት ጣራ፡ ወይም ቆሻሻው በሚገኝበት ቦታ ላይ፡ እየታጠቡ፡ ትሎች እና ጀርሞች፡ እና ሁሉም ነገር፡ ወደ ጉድጓዱ ውስጥ እንደሚታጠብ መገመት ትችላላችሁ?

89 አሁን፡ ይህ የማንኛውም አይነት ሰው-ሰራሽ ስርዓት ፍጹም ምሳሌ ነው። ሲጀመርም፡ ውድቀት ነው። አዳኝ የሚያስፈልገው ለዚህ ነው። ራሱን ማዳን አይችልም፡ ምንም ማድረግ አይቻለውም። ከጅማሬው፡ ጠፍቷል። በኃጢአት፣ በዓለም የተወለደ፣ ውሸት እየተናገረ ወደ ዓለም የመጣ ነው። ሲጀመር፡

ውሸታም ነው፡ ታዲያ በአለም ውስጥ እንዴት ለራሱ የሆነ ነገር ማድረግ ይችላል? ቅዱስ ሰው እንዴት ይሆናል?

90 ቅዱስ ሰው የለም። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የለችም። ቅዱስ መንፈስ እንጂ! ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሳይሆን፡ ቅዱስ ሕዝብ፡ በሰዎች መካከል ያለ መንፈስ ቅዱስ ነው፡ ያ ነው። ኣሜን። ጴጥሮስና ሌሎች የቆሙበት ቅዱስ ተራራ አይደለም፡ ተራራው ቅዱስ አልነበረም። ነገር ግን በተራራው ላይ የነበረው፡ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው፡ የቀደሰው። ቅዱስ ሰው አይደለም፡ በዚያ ሰው ውስጥ ያደረው መንፈስ ቅዱስ ነው፡ ቅዱስ የሚያደርገው። ሰውዬው አይደለም፡ የመንፈስ ቅዱስ አካል ነው! ሰውየው አይደለም፡ ሰው ብቻ ነውና፡ "በኃጢአት ተወልዶ፣ በዓመፅ ተጸንሶ፣ ውሸት እየተናገረ ወደ ዓለም የመጣ ሰው ነው።"

91 ማንኛውም ሰው-ሰራሽ ሥርዓት በዚያ ውስጥ ያቆየዋል። ነገሮቹን ከጠቢባን አይኖች፡ ጥበበኞች ነን ከሚሉ ይሰውረዋል፡ እነርሱም አሳባቸው "እኔ የቤተክርስቲያን ነኝ፡ ስሜ በመጽሐፉ ላይ ነው። **ይህን** አድርጌአለሁ። አባቴ **ይህ** ነበር፡ ወዘተረፈ።" ያ ጥሩ አሳብ ነው፡ ደግሞም፡ ነው፡ ምንም ተቃውሞ የለኝም። ይሁን እንጂ፡ ወዳጄ፡ ኢየሱስ ሲናገር፡ "ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር፡ ማየት እንኳ አይችልም ብሏል፡" **ልብ በሉ**፡ ይህ ማለት፡ በዓይኑ ያያል ማለት አይደለም፡ ነገር ግን፡ "የመንግሥተ ሰማያትን **መረዳት** ነው።" በውስጡ እስክትወለድ ድረስ!

92 እንዴት ነው ይህ የባፕቲስት ወንጌላዊ፡ ያ ሰው እዚያ ቆሞ ይተች እና ያፌዝ የነበረው? እያችሁ፡ ይሄን ሊቀበል የሚችል ነገር በርሱ ዘንድ አንድም ነገር የለም፡ ይህን የሚያደርግ ግን እግዚአብሄር ነው፡ እያችሁ። መንፈስ ቅዱስ የሰጠው እግዚአብሔር ነው። ይህ ግብዝነት ሳይሆን፡ ቃል መሆኑን ገለጠ። የሚሰማው ከትምህርት ቤት ሀሳብ አንጻር ነው፡ የእግዚአብሔርን በረከቶች ሁሉ—ወሰደው፡ የድሮ ዘመን ለማስመሰል ይጥራሉ።

93 በቅርብ ጊዜ፡ አንድ ወጣት የባፕቲስት ሰባኪ፡ እዚህ ጠዋት እዚህ ተቀምጦ፣ ወደ'ኔ መጥቶ፡ እንዲህ አለኝ፡- "ወንድም ብራንሃም፣ እያደረክ ያለኸው አንድ ነገር የተሳሳተ ነው።"

እኔም "ባክህ አግዘኝ፡" አልኩት።

94 እርሱም "አንተ፡ እኔ እንደማስበው አንተ ቅን እና ጥሩ ሰው ነህ፡ ግን... "

"አመሰግናለሁ ጌታዬ፡" አልኩት።

"ይሁን እንጂ በተሳሳተ መንገድ የምታደርገው አንድ ነገር አለ፡" አለኝ።

"ጌታ አንድ ስህተት አገኘብኝ ብዬ ተሰፋ አደርጋለሁ፡" አልኩት።

95 እርሱም "እንግዲህ፡ አንተ... የምታደርገው ስህተት ይህ ነው፡" አለኝ። እንዲህ አለኝ፡- "ሐዋርያዊ አገልግሎትን ለዓለም ለማስተዋወቅ እየሞከርክ ነው፡ እና፡" "ሐዋርያዊ አገልግሎት ከሐዋርያት ጋር ቀርቷል፡" አለኝ።

96 "እንደ ባፕቲስት ለባፕቲስት፡ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ፡" አልኩት።

"ምንድነው፡" አለኝ?

97 "የእግዚአብሔር ቃል በሙሉ በመንፈስ ምሪት የተጻፈ ነው፡ ብለህ ታምናለህ፡" አልኩት?

"እንዴ፡ በትክክል፡" አለኝ።

98 እንዲህ አልኩት፦ "ከዚያም፡ እንዳለ፡ 'አንድ ቃል አትጨምር፣ ወይም አትቀንስ።' ብሏል፡" ያን ጊዜ እንዲህ አልኩት፡ "እኔ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን፡ በሕዝቡ ላይ የመጣው ሐዋርያዊ በረከት አሳይሃለሁ፡ አንተ ግን የእግዚአብሄርን የቃል ኪዳኑ በረከት ከህዝቡ መቼ እንደተለየ አሳየኝ። እየህ፡ ይሄን ከቃሉ ማምጣት ካልቻልክ፡ እረፍ—ዝም በል፡ አየህ፡" "አሁንም ቀጥሏልና፡" አልኩት።

99 ለጥቂት ደቂቃዎች ዝም አለ። እኔም አልኩት፦ "እንግዲህ፡ ወንድም፡ ይህን ልጠይቅህ፡ እወዳለሁ። ጴጥሮስ በበዓለ ሃምሳ ቀን፡ ሐዋርያዊውን መልእክት አስተዋውቋል። ኢየሱስ የሰጠው የመንግሥቱ ቁልፎች ስለነበረው፡ ይህ እውነት መሆኑን፡ ሁላችንም እናውቃለን። እና አሁን የተናገረውን ተመልከት። እንዲህ አለ፦ 'ንስሐ ግቡ፡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ፡ እያንዳንዳችሁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ። የተሰፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ፡ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉት ሁሉ ነውና።' ከዛ የተዛነፈበት ቦታ ካለ፡ ታዲያ ጴጥሮስ በጴንጤቆስጤ ቀን የተናገረው ቃል ምን ሆነ? " እየህ? መቼም፡ በፍጹም አልቆመም!

የሚሞት በግ ሆይ፡ ክቡር ደምህ
ኃይሉን አያጣምና በፍጹም፡
የተዋጁ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን
ኃጢአት ላይሰሩ፡ እስኪድኑ ድረስ።

ከዚያ በተከበረ፡ በጣፋጭ ዝማሬ፡
ለማዳን ኃይልህን እዘምራለሁ፡
ይህ ምስኪን፡ የሚንተባተብ አንደበት፡
በመቃብር ውስጥ ፀጥ እስኪል ድረስ።

100 አምኜ እንድጠጋው፡ ሁላችንንም፡ ከጎኑ እንድንቆም እግዚአብሔር ይርዳኝ፡ የእውነት ወንጌል ነውና! የሰ፡ ሰር።

101 ብልህ ሰው እነዚህን ነገሮች ፈጽሞ መመልከት የለበትም። እንደማይሰሩም ይወቅ። ሠርተው አያውቁም። ተቋም የሆነ ሀይማኖት እና የተቋም ልምምድ በእግዚአብሔር ፊት በጭራሽ አይሰራም። ሳይበረዝ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ፡ መምጣት አለበት። እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን ሥርዓት ተጠቅሞበት አያውቅም፡ ከዚህ በፊትም አንድም ጊዜ የለም። አቤት፡ እናንተ፡ አባሎች እና ብዙ ነገሮች አሁንም ትመዘግባላችሁ። እውነተኛው የእግዚአብሔር ዘር፡ በበዓለ ሃምሳ ቀን እንደወረደው በረከት ግን፡ በመወለድ ይመጣል፡ ዳግመኛ በመወለድ ይመጣል እንጂ፡ በድርጅት ፈጽሞ አይመጣም።

102 እስራኤልን—እንደ ምሳሌ ለመጠቀም ተጋብዘናል፡ እንዲሁ ነበሩና። አስተውሉ፡ "የተሰጣቸውን ምንጭ፡ ትተውታል፡ ለራሳቸው ጉድጓዶችን ቆፍረዋል።" እ—እ—እ—እንደዚህ ያለ ነገር መገመት ትችላላችሁን፡ አንድ ሰው ከማያቋርጥ ምንጭ፡ እየጠጣ፡ እያችሁ፡ ለራሱ ሌላ የሚጠጣበት ጉድጓድ፡ ይቆፍራልን? እንግዲህ ነቢዩ ያለው ይህ ነው፡ የእግዚአብሔር ቃል ያለው ይህ ነው። እግዚአብሔር ለነቢዩ የተናገረው ይህንኑ ነው።

“እኔን የሕይወትን ውኃ ምንጭ—ትታችሁኛል፡ ረስታችሁኛል፤ የተሰበሩና፡ የሚያፈሱትን ጉድጓዶች፡ ለራሳችሁ ቆፍራችኋል።”

103 ልብ በሉ፡ የሚቆጣጠሩት ነገር፡ ወይም፡ የሆነ ነገር ማድረጋቸውን ማሳየት ይፈልጋሉ። የተደራጀ የሐይማኖት ሞኝነት—ይህ ነው። ሁልጊዜ መሞከር ነው፡ ከራሳቸው የሆነ ነገር ሊኖራቸው ይፈልጋሉ። ስርዓቶች ሁሉ እና ማህበረሰብ፡ እና “እኔ **የእከሌ** ነኝ፡” የመሳሰሉ ነገሮችን መያዝ ይፈልጋሉ። ትሑት የእግዚአብሔር ልጆች ከመሆን ይልቅ፡ ራሳቸውን የሚያሳዩበትን ነገር ይፈልጋሉ። እግዚአብሔር በራሱ መንገድ እንዲያደርገው ከመፍቀድ ይልቅ፡ በራሳቸው መንገድ ሊያደርጉት ይፈልጋሉ። እና ስርዓቶች ዛሬ ቤተክርስቲያንን የያዙበት መንገድ በዚህ ነው። እያንዳንዱ ስርዓት… ተመሳሳይ አይደለም፡ አንደኛው **በዚህ** መልኩ፡ ሌላኛው **በዚያ** መልኩ ይፈልገዋል። ሜቶዲስት ከሆንክ **በዚህ** መልክ መሆን አለበት። ባፕቲስት፡ **በዚህ** መንገድ። ፕሪስባይቴሪያን፡ ካቶሊክ፡ ምንም ይሁን ምን፡ ሥርዓቶች አላቸው። እኔ የምናገረው ለመቃወም አይደለም፡ ለዚያ አይደለም።

104 ሰው የሚሠራበትን የራሱ መንገድ ይፈልጋል፡ እግዚአብሔርም የሚሠራበት መንገድ አለው። “የገዛ መንገዳችሁ፡ የተሰበረውን ጉድጓድ ይዛችኋል፡ መንገዴን፡ የሕይወትን መንገድ አልፈለጋችሁትም፡” አላቸው።

105 ዛሬም ተመሳሳይ ነገር ነው፡ ትንሽም አልተቀየረም። ንጹሕ ውኃ የሚፈልቅበትን የምንጭ ውኃ ትቶ ከዚያም ራሱ ወደ ሠራው ወደ ሰባራው ጉድጓድ፡ ለመሄድ የሚፈልግ ሰው እንዴት ሞኝነት እንደሆነ አስቡት፡ ጉድጓድ ለራሱ ይቆፍራል፡ በጋጣው አናት ላይ ካለው ቆሻሻ ታጥቦ ይሞላል፡ ከዚያም ይጠጣበታል። በእርግጥ ሰውዬው ላይ የአእምሮ ችግር አለበት።

106 ቅዱስ ቃል እየገለጠ እውን የሚያደርግ መንፈስ ቅዱስ—ከመቀበል ይልቅ፣ አንድ ሰው ከቤተ ክርስትያናዊ የቅዱስ ቃል ጽንሰ ሀሳብ ጋር ሲጣበቅ፣ በዚያ ሰው ላይ የሆነ መንፈሳዊ ስህተት አለ። ትክክል ነው። በእርግጥ፡ መንፈስ ቅዱስ! ሁላችሁም ትክክል ነው ብላችሁ የምታስቡት፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ አለ። እግዚአብሔር ግን የእናንተን እርዳታ አይፈልግም። እግዚአብሔር የእናንተን ትርጓሜ አይፈልግም።

107 እግዚአብሔር የራሱ ተርጓሚ ነው። እግዚአብሔር ፍቺውን የሚያደርገው—እኔ አደርገዋለሁ ባለው መንገድ ነው። ጌታ በመጀመሪያ፡ “ብርሃን ይሁን አለ፡” ብርሃንም ሆነ። ያ ምንም ትርጓሜ አያስፈልገውም። እግዚአብሔር ያደረገው ይህ ነው። “ድንግል ትፀንሳለች፡” አለ፡ ጸነሰችም። ሌላ ትርጓሜ አያስፈልገውም። “መንፈሱን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈሳለሁ፡” ብሎ ተናገረ አፈሰሰው። ምንም አይነት ትርጓሜ አያስፈልገውም። እግዚአብሔር የገዛ ቃሉን በማረጋገጥ፣ በመግለጥ፣ እና በማረጋገጥ ይተረጉመዋል።

108 ነቢይ የእግዚአብሔር መሆኑ የሚረጋገጠው በዚህ መንገድ ነው። አለም፦ “ከእናንተ መንፈሳዊ፡ ወይም ነቢይ የሆነ ማንም ቢኖር፡ እኔ እግዚአብሔር ራሴን በራእይ እገልጥለታለሁ፡ በሕልምም እናገራለሁ። የሚናገረውም ከተፈጸመ፡ ፍሩት፤ ካልተፈጸመ ግን፡ አትፍሩት።”

109 እግዚአብሔር ቃሉን ሲናገር ተመሳሳይ ነገር ነው፡ ሰውየው “ቃሉ **እንዲህ** ነው፡” ካለ፡ በዚያ መንገድም ከተፈጸመ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።

110 እርሱ ግን “**በዚህ** መንገድ ነው፡ ዘመኑ አልፎበታል፡” ቢል፡ ነገሩ ሁሉ ያወርደዋል… ዳቦ ላጡ፡ ለተራቡ ህጻናት፡ በእጁ እንጀራ ሊሰጥ፡ ዘርግቶላቸው፡ እጁን ይመልሰባቸዋል። ይህ የምንጭ ውኃ እያለላችሁ ከጉድጓድ መጠጣት ለምን ያስፈልጋችኋል?

111 አሁን የሕይወት ምንጭ ምንድን ነው? የሕይወት ምንጭ፣ የሕይወት ውኃ ምንጭ ምንድን ነው? ከምንጭ ውኃ ጋር፡ እንድናመሳስለው እፈልጋለሁ።

112 አሁን በጉድጓድ ውኃ እና በህይወት ውኃ ምንጭ መካከል ያለውን ልዩነት እንድታስተውሉ እፈልጋለሁ፤ የምንጭ ውኃን፡ እና ነፍሳት፣ እንሽላሊቶች፣ እንቁራሪቶች፣ ጀርሞች፣ ወዘ-ተረፈ፡ ያሉበት ያረጀ የተሰበረ ጉድጓድን አስቡ።

113 እዚህ ጋር የምንጭ ውኃ አለ። አሁን ተከታተሉ። ራሱን በራሱ-የሚደግፍ ነው። ትልልቅ ሰርዓቶች እና ምንም አይነት መዋዕለ ነዋይ ማፍሰስ አይጠበቅባችሁም። ብዙ አባላትን ማስመዝገብ አያስፈልጋችሁም። በውስጣቸው በሚሰራው፡ በሕይወት መንፈስ፡ አባላቱን ይደግፋቸዋል።

114 ከእሱ የሚመጣውን ውኃ፡ ንጹህ፣ ኩልል ያለና፣ ፍሬሽ እንደሆነ አስተውሉ። የጉድጓድ አይደለም፡ በአርባ እና በኃምሳ የተለያዩ አእምሮዎች፡ እንዲህ የተጻፈ፡ “**ይህ** ልክ ነው፣ **ያም** ልክ ነው፣ **ይህ** ጽንሰ ሀሳብ ነው፡” በማለት፡ ለምርጫ የሚጠራ፡ ካደረጉ በኋላ፡ የሐይማኖት ተቋም የሚመሰረትበት ጉድጓድ አይደለም። ከእግዚአብሄር እጅ የወረደ፡ ኩልል ያለ እና ንጹሕ፡ ያልተበረዘ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ትክክለኛ የምንጭ ውኃ ነው።

115 ልብ በሉ፡ የኃይሉ ምስጢር በራሱ ውስጥ ነው። ሰው ሊያገኘው አይችልም። ከበታችሁ፡ የተለየ ግፊት፡ ወደ ላይ እንዲገፋ ያደርገዋል።

116 የኢንዲያና ግዛት ደን ጠባቂ በነበርኩበት ጊዜ፡ አስታውሳለሁ፣ በሃሪሰን ካውንቲ እመላለስ ነበርና፡ ጅረት ነበረ፡ ምንጭ፡ ሁልጊዜም ይፈልቃል። እና ልክ፡ አቤት፡ ከማንም ይልቅ ደስተኛ ይመስላል። በረዶው መሬት ላይ ይሁን፡ በረዶ ግግር ይሁን፡ ይቀዝቅዝም፡ ይብረድም ዝም ብሎ ይፈልቃል፤ አሮጌው ሰው ሰራሽ ኩሬዎች እና ማጠራቀሚያዎች ግን፡ ከነ እንቁራሪቱ ከነኀዙ፣ ጠጣራ በረዶ ጋግሮ ቁጭ ይላል።

117 ያ ደግሞ የትኛውም የሐይማኖት ተቋም፡ በትንሽ የመንፈስ እጦት ወይም በትንሽ ድባብ ለውጥ እንደሚበርድ ያሳያል። የእግዚአብሔር የምንጭ ጅረት ግን፡ ትናንትና፡ ዛሬም፡ እስከ ዘለአለም—ያው ነው፡ ሁሉንም ነገሮች ከውስጡ እየገፋ ከውስጡ ያወጣቸዋል። ከመጀመርያም ጀምሮ፡ በውስጡ ሌላ ነገር የለውም። ምንም ነገር ቢገባበትም፡ ተገፍቶ ይወጣል።

118 አንድ ቀን በዚያ ቁጭ ብዬ፡ እንዲሁ እየተፍለቀለቀ ነበርና፡ እንዲህ አልኩኝ፡ በአሳቤ፡ “እስኪ ለአፍታ ያህል፡ ከዚህ ምንጭ ጋር ልነጋገር።” ኮፍያዬን አውልቄ፡ እንዲህ አልኩት፡- “ደስተኛ ያደረገህ ምንድነው? ስለምንድን ነው የምትፍለቀለቀው? ምናልባት አልፎ አልፎ፡ አጋዘኖቹ መጥተው ከአንተ ስለሚጠጡ ነውን።”

መናገር ቢችል ኖሮ፡ “አይደለም፡” ይለኝ ነበር።

“ወይስ እኔ ከአንተ ስለጣጣሁ ነው፡” አልኩት።

“አይ፡ ያ አይደለም።”

119 አልኩትም፡- “አንተን፡ ኩልል ያልክ፡ ንፁህ ያደረገህ ምንድን ነው? እና ምን—ሁል ጊዜ በደስታ እየተሞላህ፡ እየሳቅህ፡ እንድትፍለቀለቅ የሚያደርግህ፡ ማንም የማያቀዘቅዝህ ነገር ምንድን ነው? አየር ላይ ትዘላለህ፡ ከንጹሕ ውኃ በቀር፡ ሌላ የለህም።”

120 ሊያናግረኝ ቢችል ኖሮ፡ ጅረቱ ምን እንደሚል ታውቃላችሁ? “ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ የምፍለቀለቀው እኔ አይደለሁ፡ ከበስተኋላዬ፡ እንድፍለቀለቅ የሚያደርገኝ ነገር አለ፡” ይለኝ ነበር። ከዚህም ጋር ያው ነው… ደካማ ቃል ቢሆንም፡ ለማለት የፈለግኩትን ገብቷችኋል።

121 የዳግም-መወለድ ልምምድም ያው ነው። ልትቆጣጠሩት አትችሉም። ወደ ዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ፡ የውኃ ምንጭ—ጅረት ነው። አያችሁ፡ እናንተ ማድረግ የማትችሉት የሆነ ነገር አለው። ሰው-ሰራሽ ማጠራቀሚያዎች በረዶ ሊሆኑ ይችላሉ፡ ከዚያም ሪቫይቫልን እና ሁሉንም ነገር ይለምናሉ፡ በምንጭ ስር ያለ፡ በምንጭ ውስጥ የሚኖር ሰው ግን፡ ቀንና ሌሊት ያው ነው! በጭራሽ፡ ወቅታዊ ዝናቦችን እና ወቅታው ሪቫይቫሎችን አትጠብቁ። በሁሉ ተሞልታችኋል። “በውስጡ፡ የማያቋርጥ፡ የህይወት ምንጭ እሰጠዋለሁ።” በውስጡ የሆነ ነገር አለ፣ በየቀኑ ፍሬሽ፣ ንጹህ እና ኩልል ያለ ነው። እራሱ ለራሱ ማረጋገጫ እያደረገ፡ ሰለራሱ የሚመሰክር፡ ያልተበረዘ የእግዚአብሔር ቃል በልባችሁ እና በአፋችሁ ውስጥ ነው። ዝናብም ሆነ፡ በረዶ፡ ምንም ዓይነት የአየር ሁኔታ ይሁን፡ አያስጨንቀኝም፡ አሁንም መንፈስ ቅዱስ ከውስጣችሁ ስለሚፈልቅ ደስተኞች ናችሁ። ልብ በሉ። የተሰወረው ኃይል እርሱ ነው። ኦህ፡ ምስጢሩ በውስጡ አለ።

122 ለሚጠጣው እና ከሙላቱ ለሚጠቀም ሁሉ፡ ራሱን፡ በነጻ ይሰጣል። ከእንግዲህ እየወጣችሁ፡ እንዲህ አትበሉ፡- “አሁን፡ እኔ ሜቶዲስት ስለሆንኩ ሪቫይቫልን ፍለጋ፡ ወደ ሜቶዲስት ቤተ ክርስትያን ልሂድ። **እዚህ** መሄድ አለብኝ፣ ግን (ከሆነም) የጴንጤቆስጤ ሪቫይቫሊስት ስለሆንኩ ወደ ጴንጤ መሄድ አለብኝ።” እላችኋለሁ፡ ያን የምንጩ ውኃ ጅረት፡ ያን ፏፏቴውን ስታገኙት፡ ከዚያም ስትጠጡ፣ ምንም ልዩነት አይኖራችሁም፡ ለሚመጣው ሁሉ ትሰጣላችሁ። የህይወት ተስፋን ለካቶሊክ፡ ለፕሮቴስታንት፡ ለአይሁዳዊ፡ ለኤቴስት፡ ወይም ለማንኛውም ነገር ለመስጠት ፍቃደኛ ትሆናላችሁ። በእውነቱ፡ በውስጣችሁ የሚሰራ፡ እውነተኛ የሆነ ነገር አግኝቷችኋል።

123 ሌላው ደግሞ ልብ ማለት ያለባችሁ፡ መቅዳት መናጥ አይጠበቅባችሁም። መጎተት፡ እና መቅዳት አይገባችሁም። አንዳንዴ እስኪያቅለሸልሸኝ ድረስ የሆነ ነገር ለማውጣት፡ ብዙ ጉተታዎች አያለሁ፤ ብዙ መዝሙር ማብዛት፡ እና ወደ-ላይ እና ወደ-ታች መዝለል፣ ወይም—በከተማው ውስጥ “የዘመኑ ሰው” የሚል ብዙ የሰነ ጽሑፎች፡ እና ግዙፍ ታላላቅ ማስታወቂያዎች ይደረጋሉ።

124 የዘመኑ ሰው አንዱ ብቻውን ነው፡ እሱም ትላንትናም፡ ዛሬም፡ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው የሆነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነ አንድ መልእክተኛ አለ፡ እሱም—ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። የሰ፡ ስር።

125 ይህንን ማንሳት ወይም መጎተት የለባችሁም። ወይም፡ አያስፈልግም፡ መቀላቀል የለባችሁም። ዝም ብላችሁ፡ በነጻ ተቀበሉት። አሜን። “እኔ የህይወት ውኃ ምንጭ ነኝ፡ የራሳችሁ ጉድጓዶችን ለመስራት፡ እኔን ትታችሁኛል።”

ከእንግዲህ ምንም ነገር መጎተት፡ መጎተት፡ መሳብ፡ መቀላቀል፡ መቆፈር፡ አያስፈልግም። ዝም ብላችሁ፡ በነጻ ውሰዱ።

126 ማጣሪያ ጨርቅ፡ እንዴት እንደሚሰራ የሚነግራችሁ ሰው-ሰራሽ ቲኦሎጂ፡ እንዴት እንደሚያልፍ ነጋሪ፡ አያስፈልጋችሁም። ምንም። አንዳንድ የሰርዓተ ትምህርት ሰው-ሰራሽ ቲኦሎጂዎች፡ **በዚህም**፡ **በዚያም**፡ የራስ-ጽድቅ ሐይማኖት፡ ወይም አንዳንድ የሐይማኖት ሥርዓት፡ ውኃ ማጠራቀሚያዎች አያስፈልጋችሁም። መምጣትም የለባቸውም። የነተበ ጨርቅ ብታደርጉበት፡ አየር ላይ ያሽቀነጥረዋል። ከሱ ጋር በምንም አይሄድም። ራሱን-የሚደግፍ ነው! ወደ ሕይወት የሚፈልቅ የእግዚአብሔር ኃይል ነው። አንድ ሰው እንዲህ ያለውን ነገር ትቶ፡ ወደ ሰርዓት ውስጥ መግባት ለምን አስፈለገው፡ ከምለው በላይ ነው። ማጣሪያ ጨርቅ አይፈልግም። አያስፈልገውም። ለመሞላት ሌላ አይጠብቅም... ወቅታዊ ዝናብ መጠበቅ አያስፈልገውም። ዘወትር ሙሉ ነው። አሜን።

127 ሰዎች፡ "ዛሬ እኔ ቆሻሻ መጣያ ውስጥ ተጥያለሁ፡" ሲሉ ሰምቻለሁ። ኦህ፡ ማይ!

128 ኦህ፡ ነገሮች በትክክል ባይሆኑም፡ እኔ በእግዚአብሔር ፊት በመኖሬ ደስተኛ ነኝ። ሕይወቴ እሱ ነው። ኣሜን። እርሱ ሕይወታችን ነው። እርሱ ሕይወት፡ የተትረፈረፈ ሕይወት ነው። የሰ፡ ሰር። ያደረገልንን—ተመልከቱ። ኃይሉ እና ንጽህናው በራሱ ውስጥ ነው። ከውኃ ጉድጓድ ወይም ከማንኛውም ሌላ ሰርዓት መምጠጥ አያስፈልገውም።

129 አንድ ሰው ሲናገር፦ "እሺ፡ ሕበረት የምታደርግበት መታወቂያህ የነማን ነው አለ? እስኪ ጥሩ ባፕቲስት መሆንህን እንይ። መታወቂያህን ልመርምር።" ወይም—ወይም "... ጥሩ ጴንጤ... ዋንነስ ከሆንክ... ቱነሰ... ሰላሴ።" ወይም—ወይም "... ሌላ ከሆንክ።" ልብ በሉ፡ ምንም አይነት መምጠት አይፈልግም። ዘወትር የሚፈስ ነው። አዎን።

130 ታውቃላችሁ፡ የራሴ የቆየች ጉድጓድ ነበረችኝ፡ ውኃ አፈስበታለሁ ከዚያ በኋላ፡ ውኃውን ለማውጣት፡ ባረጀ ቱቦ፡ ደጋግሜ እመጠዋለሁ እመጠዋለሁ አሁንም እመጠዋለሁ፡ እንደው፡ ተጨማሪ ውኃ አፈስበታለሁ፡ ነፍሳት እና ልዩ ልዩ ተቀላቅለው ይገባሉና፡ ነፍሳት እና ሌሎች ነገሮች ይወጣሉ። እነዚህ አንዳንድ ሰልታዊ ሪቫይቫሎችም ሁኔታቸው ይህ ነው።

131 ግን እግዚአብሔር ይመስገን "ኃጢያተኞች ከደሙ በታች የሚጠልቁበት፡ በደም የተሞላ ምንጭ አለ!" እነሱም ወደዚያች ምንጭ በመጡ ጊዜ ክርስቲያኖችን ታደርጋላችሁ እንጂ፡ የቤተ ክርስቲያን አባላት ማድረግ አትችሉም።

132 የሕይወትን ውኃ ምንጭ ትታችሁ፡ እንዴት እንደዚያ ካለው የገንዳ ውኃ ትጠጣላችሁ?

133 አይጎተትም፡ ኃይሉ በራሱ ውስጥ አለ። መመጠጥ አያስፈልገውም፡ የሰ፡ ሰር፡ (የገዛ) ህይወቱ በውስጡ ይኖራልና። የእግዚአብሔር ዘር በሰው ልብ ውስጥ እንደዚህ ነው። የእግዚአብሔር ሕይወት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሳይሆን በግለሰብ ውስጥ ነው, በውስጥህ፡ በአንተ ውስጥ ነው፡ የህይወት ዘረ መል ያለህ አንተው ነህ።

134 አንዲት ቅምሻ ብቻ ሁሉም ዓይነት ቀሳውስት ታረካለች። የካቶሊክን ቄስ ጠይቁ፡ ባፕቲስቱን ጠይቁ፡ ሌላውም ምንም ይሁን። የዚህ ታላቅ እና ፍሬሽ ጅረት ውኃ የምንጭ ቅምሻ ብቻ፡ እላችኋለሁ፡ እውነት ነው ያረካል። ለተራበች ነፍስህ፡ ለማንኛውም፡ ለተጠማ፡ ለማንኛውም አርኪ ነው። አሁን ካልተጠማችሁ... ይህ ታናሽ ባፕቲስት፡ ከመጀመርያም፡ አልተጠማም ነበር፡ በተጠማ ጊዜ ግን፡ ውኃው ግሩም ጣዕም አለው። ትክክል ነው፡ ግን መጠማት አለባችሁ፡ "የተባረከ ጥማት፡" ኢየሱስ እንዳለው። "ጽድቅን ስትራቡና ስትጠሙ ብፁዓን ናችሁ፡ ትጠግባላችሁና።" ኣሜን። ወዳጄ፡ ኢየሱስ እንደዛ ብሏል። የሰ፡ ሰር፡ ለተጠማ ሰው ብሩክ ምንጭ ነው።

135 ሰው ግን ለምን ይሄን ወደ ረግረግማ መቀየር ይፈልጋል? የምንጭ ጅረትን በረግረግ ለመቀየር እንዴት ትፈልጋላችሁ፡ በሰው-ሰራሽ አሳቦች የተሰሩ ልዩ ልዩ ብክለቶች እና ነፍሳት፡ እግዚአብሄር ራሱ "ቃሉ ላይ የሚጨምርም፡ ሆነ ከቃሉ አንዲት ነገር የሚቀንስ፡ እጣ ፈንታው ከህይወት መዝገብ ይወገዳልል አላለምን"?

136 እግዚአብሔርም ይህን ቃል በትውልድ ሁሉ እንደሚያረጋግጥ ቃል በገባ ጊዜ፡ "የተሰፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ፡ ጌታ አምላካችንም ለሚጠራቸው፡ በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና፡" ለብዙ ዓመታት ከተበከለው፡ ካረጀ መና፡ ሰልታዊ ጉተታ መጎተት ለምን ያስፈልጋችኋል? መናው ይሁን ችግር የለውም፡ አልቃወመውም፡ የማርቲን ሉተር ዘመን፣ **የዚያ** ዘመን፣ **የሌላኛው** ዘመን፣ እና ሌሎች ተሐድሶዎች፣ አልቃወመውም፤ ይሁን እንጂ ከረጅም ጊዜ በፊት የወረደ መና ነው።

137 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካስተዋልን፡ በየቀኑ ይለቅሙት ነበር። አዲስ ይለቅሙ ነበር። ትንሽ ካረጀ በኋላ ይበሰብሳል። ሳይፈራርስ ሊበሰብስ አይችልም። እንዲበሰብስ—በውስጡ ባክቴሪያ፡ ወይም የሆነ ነገር ሊኖረው ይገባል። ያ እንደሆነ እናውቃለን።

138 ሰርኦቶቹም እንዲሁ ናቸው! ከአንዱ ታላቅ ሪቫይቫል ወደ ሌላው ካለፈ በኋላ፣ ይበከላል ብዙ ነፍሳት ይፈጥራል፡ እንደተባለውም፡ የሚወዛወዝ-ጭራ የተሞላ፡ ትንንሽ ነፍሳት የሚርመሰመሱበት ያረጀ ጉድጓድ ይሆናል።

139 ዛሬም የብዙ ሰዎች ልምምድ ጉዳይ ይህ ነው። በሚወዛወዝ-ጭራ የተሞሉ ብቻ—ናቸው፡ ከአንዱ ወደ አንዱ፡ እና ከአንዱ ወደ ሌላው ይወዛወዛሉ፡ ምንም እውነት የሌላቸው ተረቶች ይናገራሉ። ልክ ነው፡ ከአንዱ ወደ ሌላው መወዛወዝ ብቻ። "ሜቶዲስት ነበርሁ፡ ባፕቲስት ተቀላቀልሁ። ካቶሊክ ነበርሁ፡ **ይህን** ለመሆን ሄድኩ። **እንደዛ** ለመሆን ሄድኩ።" የሚወዛወዝ-ጭራ ብቻ ነው።

140 ኦህ፡ ሌላውን ሁሉ ረስታችሁ፡ ወደ ምንጩ ተመለሱ (አሜን!)፡ ወደ ጅረት ምንጩ፡ ሕያው-ወደ ሆነው የክርስቶስ መገኘት! የማይጠፋ የሕይወት ምንጭ እንደሆነ እምነዋለሁ። እሱን አብዝታችሁ በወሰዳችሁ ቁጥር፡ የበለጠ ፍሬሽ፡ የተሻለ ቃዝቃዜ፡ በብዙ የተሻለ ይሆናል፡ የበለጠ ጣፋጭም ይሆናል። አሁን እሱን ለሠላሳ-ሦስት ዓመታት ሳገለግል ቆይቻለሁ፡ እያንዳንዱ ቀን ካለፈው ቀን የበለጠ ጣፋጭ እየሆነ ይሄዳል። ከዚህ ውሃ ብትጠጡ መቼም አትጠሙም እንዳለ... መቼም አልተጠማሁም። ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ልብ በሉ። ኦህ!

141 እስራኤል ዛሬ ብዙዎች እንደሚያደርጉት አደረጉ፡ የውኃውን ምንጭ ትተው ጉድጓዶችን ይቈፍሩ ዘንድ ሄዱ።

142 አሁን ስለ ጸጋው ትንሽ ለመናገር ያህል፡ የእግዚአብሔር ጸጋ ምንድነው ነው። እንግዲህ ብዙ ሕጎች እና የሕግ-ዘርፎች አሉ፡ “በዚህ መስፈርት ካልተለካ... እኔ የሐይማንኖት መለኪያ አለኝ፣ አንተም በዚህ መለኪያ ካልለካህው፡ መግባት አትችልም፡ እንዲህ እና እንዲያ፡” እና ወዘተረፈ። እግዚአብሔር ግን የሚያድነን በጸጋ እንጂ፡ በመለኪያ ዘንግ አይደለም። አያችሁ? ነገር ግን፡ እግዚአብሔር አሁን ስለ ጸጋው ሲናገር፡ ይህ እንዴት እንደሚሆን፡ ከእርሱም በመጠጣት፡ ከዚህ የመለኪያ እንጨት...

143 እስራኤል አጉረመረመ፡ አጉረመረመ። ልብ በሉ፡ “እንደገና እጎበኛችኋለሁ፡” አላቸው። በቅዱስ ቃል ውስጥ አስተውሉ። አስተውሉ፡ እንደገና ሊፈትናቸው፡ ሊጎበኛቸው ነው። አጉረማራሚው እስራኤል፡ በቀይ ባህር፡ በግብጻውያን የማይንቀሳቀስ ውኃ አልፎ፡ ነጻ ህዝብ ለመሆን፡ እርሱን እንዲከተሉ ተጠሩ። ባርያዎች ነበሩ። አሁን ከእርሱ ጋር፡ ነፃ ሕዝብ እንዲሆኑ ተጠሩ። በሙት ባሕር፡ በሙት ባሕር በኩል፡ ማለት፡ በቀይ ባህር፡ ወጥተው፡ ወደ ምድረ በዳ ሊገቡ፡ ይህም ከመካከላቸው አስመሳይ የነበሩትን፡ ሳይገረዙ ለማስመሰል ከሚሞክሩት ለመለየት ነበር።

144 ኦህ፡ ችግር የፈጠረውም ያ ነበር። ፎርዖን እና ሰራዊቱ ሁሉንም በዚያ በበረሃው-... ፡ ማለት፡ በዚያ—በባሕር ውስጥ፡ ጠፉ። ሰዎች ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ሃይል ሲራመዱ አይተዋልና፡ በበረከቱ ውስጥ ያልተካተቱ ሰዎች ወደ ኋላ ተመልሰው፡ መጥተው ያንን ለማስመሰል ሞከሩ። በሞከሩ ጊዜ ግን፡ ሁልም ጠፉ። ያም ስጋዊ ንጽጽር ነበር።

145 ያንን ለማድረግ የሚሞክር፡ አንድን ነገር ለመምሰል የሚሞክር ሰው፡ የእውነተኛውን ክርስቲያን ሥጋዊ ንጽጽር እያደረገ ነው።

146 እዚያ ያለው ህንዳዊ ወንድሜ ያውቀዋል። በቦምቤይ ዙሪያ ኑ እና እዚያ ያሉትን ሰዎች ታያላችሁ፡ ሂንዱዎች እና ሌሎች፡ ስለት ላይ የሚተኙ... ስባሪ ብርጭቆዎች ላይ እና—እና እሳት ላይ የሚራመዱ፡ ምን ማድረግ እንደሚችሉ እና የመሳሰሉትን ለማሳየት ነው... ጫካ ውስጥ የሚኖር የሥጋዊ ሰው ማስመሰል ናቸው፡ ያንን የሚያደርገው ለጣኦቱ ለመሰዋት ነው።

147 እነዚህን ስጋዊ ማስመስሎች፡ አንዱ ሌላውን የመምሰል ሙከራዎች፡ በሁሉም ሐይማኖቶች ህይወት ውስጥ አይተናቸዋል። እናንተ ልትሆኑት የሚገባችሁ አንድ ምሳሌ አለ፡ ቃል እንደ ሆነው፡ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ከዚያ የእግዚአብሔር ቃል ወደ እናንተ ሲመጣ፡ ተመሳሳይ ነገር ይሆናል።

148 እግዚአብሔር ግን፡ እንዲሁ በቀጥታ ወደ ተስፋይቱ ምድር መራቸው። እነርሱም፡ በምድረ በዳ ጉዞ በጀመሩ ጊዜ፡ ብዙ ጉድጓዶችን፡ በመንገዳቸው አገኙ፡ ከተለዩ በኋላ፡ ጉድጓዶች ሁሉ፡ በፊታቸው ደረቅ መሆናቸውን አስተዋሉ።

149 ወንድሜ ሆይ፡ አንተም ወደ ተስፋይቱ ምድር ጉዞ ስትጀምር፡ ተመሳሳይ ነገር ታስተውላለህ። በሮች ተዘግተው ታገኛቸዋለህ። ትንሹ ሰባኪ እንደተናገረ፡ ያ አንግሊካን ይሁን ሌላ እንጂ፡ እንደምታውቁት፡ በመጀመሪያ የሆነበት ነገር፣ ቤተ ክርስቲያኑ አወገዘችው። አያችሁ፡ እንግዲህ እሱ መንፈስ ቅዱስን እስከተቀበለ ድረስ፡ ፍጻሜው ነበር።

150 እኛም... እስራኤል ወደ ተፋይቱ ምድር፡ በጉዟቸው እንደ ምሳሌ፡ ተመሳሳይ ነገር እንያለን። ጉድጓዶቹ ሁሉም ደርቋል። አዎን፡ ለተሰፋ ቃሉ የመታዘዝ ጉዟቸው፣ በጉዟቸው፡ ጉድጓዶቹ፡ ደርቀው አገኙአቸው። እንግዲህ ለጉዞው፡ ያ ጉድጓድ—በጉድጓዶቹ መተማመን እንደማይቻል ተማሩ።

151 እናም የእግዚአብሔርን ቃል በመታዘዝ ከተጓዝክ፡ **ይህን** ለመቀላቀል እና **ያንን** ለመቀላቀል ሞክር፣ በአለም ውስጥ እሱን የሚደግፍ ጉድጓድ እንደሌለ ማወቅ ትችላለህ። በፍጹም የለም። ግለሰብ ነህ። እግዚአብሔር ሊመራህ በሚፈልገው መንገድ ይመራሃል። እንግዲህ፡ ዛሬም ተመሳሳይ ነገር ሆኖ እናገኛለን፡ ገንዳዎች ሁሉ ደርቋል።

152 የተሰፋው ቃላት ግን፡ ለህዝቡ የገባውን ቃል ለሚፈጽም ለእግዚአብሔር፡ ሁል ጊዜ እውነት ናቸው። የሚያስፈልጋቸው ሁሉ እንደሚያቀርብላቸው ቃል ገብቷል፡ ስለዚህም ያንን አደረገ። እስራኤል እያጉረመረመ፡ በባዶ፡ በደረቁ፡ ጉድጓዶች መካከል፡ በምድረ በዳ፡ ሲጓዝ እስቲ አስቡት! አገልጋዩ-መሪው፡ ነቢዩ ሙሴን፡ ወደ አንድ ጥግ ጠርቶ፡ እምነት የነበራቸው ልጆቹ እንዳይጠፉ፡ ከተመታው ዓለት ውስጥ፡ ውኃን አፈለቀላቸው።

153 በዚህ ዘመንም፡ ይህ ስለ ጸጋ ይናገራል። እንደኔ፡ የማይገባን ነበርን። የነገሮች አደራረጋችን፡ ኑሮአችን፡ የማይገባቸው ነገ።

154 ተመልከቱ፡ እግዚአብሔር ግን፡ በዚህ ዘመንም፡ ልክ እንደ ዛሬ ጠዋት፡ ለሜቶዲስት፣ ለባፕቲስት፣ ለፕሪስባይቴሪያን፣ ለካቶሊክ፣ እና ለሁሉም፣ ምንጭ ከፍቷል። ዕብራውያን 13 እርሱ ትናንትም፣ ዛሬም፣ እስከ ለዘላለምም ያው እንደሆነ፡ ይህን ያረጋግጣል። ስለዚህ—እውነት ነው፡ ዮሐንስ 3:16 “እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ፡ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና፡ በእርሱ የሚያምን ሁሉ፡ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ።”

155 ደግሞም የተሰቀለው በድርብ ምክንያቶች ነው፡ ሕዝቡ ስለ አጉረመረመ እና ኃጢአት ስለ ሠራ፡ በእባቦችም ተነድፈው ይሞቱ ነበርና፡ ስለ ኃጢአታቸውም ሥርየትና፡ ስለ ህመማቸው ፈውስ ነበር።

156 ዛሬም የተከፈተልን ምንጭ ይህ ነው፣ ለደህንነታችን እና ለፈውሳችን፡ ለሥጋዊ ፈውስ። “ትላንትናና፣ ዛሬ፣ እስከዘለአለም ድረስ ያው ነውና።”

157 በእግዚአብሔር የተሰፋ ቃል የተመታው አለት፡ በታዘዘ ጊዜም፡ ኩልል ያለና ንጹሕ ውኃ አፍልቆ ነበር፡ የቆመ ውኃ—አልነበረም፡ ወይም የተመረዘ አይደለም፡ እግዚአብሔር ያለበት እንጂ። ንጹሑን ውኃ፡ የጠጡት ሁሉ አዳናቸው። አሁንም ያን በብሉይ ኪዳን ውስጥ፡ እንደ ምሳሌ እናነባለንና፡ እውነት መሆኑን እናውቃለን።

158 እንግዲህ፡ አጠቃቀሙን ለመማር መጎተት፣ መቅዳት፣ መቀላቀል፣ ወደ ትምህርት ቤቶች መሄድ አያስፈልግም። እነርሱ አጠቃቀሙን እንዴት እንደሆነ ያስተምሯችኋል፡ አያችሁ፡ “ኦህ፡ እሺ፡ አንተ መንፈስ ቅዱስ፡ መሞላትህን አምነናል፡ ግን ደግሞ—መጠቀም ያለብህ **በዚህ** መንገድ ነው።”

159 አያችሁ ግን፡ እርሱ፡ ተቆጣጣሪ የለውም። መንፈስ ቅዱስ እናንተን ይጠቀምባችኋል እንጂ፡ እናንተ መንፈስ ቅዱስን አትጠቀሙበትም፡ አያችሁ። ልብ በሉ፡ እናንተን የያዛችሁ መንፈስ ቅዱስ ነውና፡ መንፈስ ቅዱስን፡

እናንተ አትጠቀሙበትም። ስጦታ እርሳስን ለመቅረጽ፡ እንደምታነሱት፡ ስለት አይደለም። እራስህን ለእግዚአብሔር አሳልፎ መስጠት እና መንፈስ ቅዱስ እንዲጠቀምብህ ራስህን ከመንገድ ማውጣት ነው።

160 አስተውሉ፡ መናጥ ወይም መቅዳት አላስፈለጋቸውም ነበር፡ ወይም "ውኃውን እንዴት እንጠቀማለን?" አላሉም፤ ምክንያቱም፡ እንዴት እንደሚጠቀሙበት ያውቁ ነበርና። ተጠምተው ነበር። ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያውቁ ነበር።

161 ወንድም ይሁን ሴት፡ እንዲሁም የየትኛው ተቋም ወይም ስርዓት ተከታይ ይሁን፡ እንዲሁ ነው። እግዚአብሔርን ከተጠማ፡ ልክ እንደዚህ የአንግሊካን ወንድም እንዳደረገው ወደ ትምህርት ቤት መሮጥ የለበትም፡ ወይም እንግሊዛዊው ወንድም፡ ትላንት ማታ፡ ወደ አንግሊካን ቤተክርስቲያን ተመልሶ፡ በልሳኖች መናገር፡ እና ያገኘውን **ይህን** ታላቅ ስጦታ፡ እንዴት መጠቀም እና ማድረግ እንዳለበት ለመመካከር እንደሄደ አይደለም። ሲጀመር፡ ያባርሩት ነበርና። አያችሁ? ስለ ተጠማ፡ እግዚአብሔር አረካው። ሌላ ነገር የለውም። ተጠማ፡ ስለዚህም ተሞላ።

162 ማድረግ ያለባችሁ የሚነግራችሁ፡ እና የሚቆጣጠራችሁ ሰው አያስፈልጋችሁም። እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው—ልሰራለት በሚፈልገው መንገድ ይመራዋል። አንተ፡ በራስህ—አንድ ግለሰብ ነህ። የእግዚአብሔር አካል ነህ። ሰፍራህን ማንም አይወስድብህም። አሁን ወደ ሌላ ሰው በመሄድ፡ "**በዚህ** መንገድ" ይሄን ማድረግ አለብኝ፡ ወይም፡ "**በዚያ** መንገድ" ያንን ማድረግ አለብኝ ማለት አያስፈልግህም። ኖ፡ ሰር። እግዚአብሔር ራሱ—በሚፈልገው መንገድ ይጠቀምበታል። በሚጠማህ ጊዜ፡ መጠጣት እንዳለብህ በደንብ ታውቃለህ።

163 ዛሬ ጠዋት የተጠማችሁ ካላችሁ፡ ከርሱ ዘንድ ጠጡ፡ ማድረግ ያለባችሁ ያ ብቻ ነው። እግዚአብሔር ለጥማታቸው፣ ለተጠሙ ልጆች ከርሱ ዘንድ በነፃነት የሚካፈሉበትን መንገድ አዘጋጅቶላቸዋል። እግዚአብሔርም ዛሬ ጠዋት ለተራበ እና ለተጠማ ለእያንዳንዱ ወንድና ሴት፡ መንገድ አዘጋጅቶላቸዋል። ምናልባት እዚህ ተቀምጠው ያልዳኑ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። እዚህ ተቀምጠው ለመዳን በቋፍ ላይ ያሉ ሰዎች አሉ።

164 እንደ ቤተ ክርስቲያን አባላት፡ እዚህ ተቀምጠው፡ በትክክል መሰራት እየፈለጉ፡ ነገር ግን ከጉድጓድ የሚጠጡ ሰዎች አሉ። እነዚህን እውነቶች በጭራሽ አይነግሯችሁም።

165 ለመምጣት ብቸኛው መንገድ፡ የእግዚአብሔርን የተሰፋ ቃል ተቀብሎ፡ ወደ ምንጭ መምጣት ነው፡ ከዚያም እርሱ ጥማትን ያረካል። "ከዚህ ምንጭ የሚጠጣ ከእንግዲህ ወዲህ አይጠማም።"

166 የራሱ የሆኑትን እንዴት ነፃ እንዳወጣ—አሁን አስተውሉ—እነርሱ ይህን ውኃ የተቀበሉት፡ በጸጋው እንጂ፡ በስርዓት ወይም በትምህርት ጉድጓድ አይደለም። ለቃሉ ማረጋገጫ መስጠቱ፡ ሕይወት-ሰጪ ምንጭ ይህ ነው። ያን ቃልና ውኃ በወሰዳችሁ ጊዜ ሕይወትን እንዳገኛችሁ ሰንቶች ታውቃላችሁ፡ ህይወት እንደተቀበላችሁ ያወቃችሁ ስንቶች ናችሁ?

167 ለምሳሌ፡ አንድ፡ ወይም ሁለት፡ ሌላ ምሳሌ፡ እንውሰድና፡ ከዚያ በኋላ እጨርሳለሁ። ያንን ቁልፍ የሆነ ቦታ ማግኘት አ—አለብኝ። ነገር ግን ልብ በሉ። ዝም ብዬ ማውራቴ፡ ለማውራት ፈልጌ አይደለሁም። አስተውሉ፡ ለምሳሌ ያክል፡ ሁለት ሰዎችን እንውሰድ።

168 በያዕቆብ ጉድጓድ፡ በተቆፈረ ጉድጓድ አጠገብ የነበረችውን ሴት እንውሰዳት። በዚያ ተቀምጣ ነበረች። ሴትየዋ ውኃ ልትቀዳ የመጣችበት ጉድጓድ፡ ይህ ጉድጓድ እንደሆነ ብቻ ታውቃለች። እና ከጉድጓዱ አጠገብ፡ በነበረው ትንሽ ገጽታ፡ አንድ አይሁዳዊ፡ በዚያ ተቀምጦ አገኘች። እሷም ሳምራዊ ነበረች፡ ከተማዋም ሲካር ትባላለች። ይህ አይሁዳዊ፡ ይህ ሰው፡ ለዚች ሴት ባልተለመደ ቃል፡ “ውኃ አጠጪኝ፡” ብሎ እንደተናገራት እናገኘዋለን።

169 እንዲህ አለች፡- “አንተ እኔን እንደዚህ አይነት ጥያቄ መጠየቅህ ትክክል—አይደለም። በመካከላችን መለያየት አለ፤ አንተ አይሁዳዊ፡ እኔም ሳምራዊት ነኝ።”

170 እሱም አላት፡- “ከማን ጋር እደምትነጋገሪ ብታውቂው ኖሮ፡ አንቺው ራስሽ ትጠይቂኝ ነበር፡ እኔም ደግመሽ ወደዚህ ጉድጓድ እንዳትመጪ የሚያደርግሽ ውኃ በሰጠሁሽ ነበር፡ በሆድሽ የሚፈልቅ ምንጭ በሰጠሁሽ ነበር።” ልብ በሉ ይህ እውነት መሆኑን ባወቀች ጊዜ!

171 አሁን፡ በመጀመሪያ፡ ማንም ሰው እንዲህ ሊል ይችል ነበር። እሷ ግን “እናንተ በኢየሩሳሌም ስገዱ ትላላችሁ እኛም በዚህ ተራራ እንሰግዳለን፡” አለች።

172 እርሱም፡- “መዳን ከአይሁድ ነው። የምናምነውን እናውቃለን። ነገር ግን፡” አላት፡ “አንድ ነገር ልንገርሽ፡” እንደዚህ ባሉ ቃላት፡- “ሰው ለእግዚአብሔር፡ በመንፈስና በእውነት እንጂ። በዚህ ተራራም ወይም በኢየሩሳሌም የማይሆንበት ጊዜ ይመጣል፡ አብ እንደዚህ ያሉትን ይፈልጋልና።” “ሂጂና ባልሽን ይዘሽ ወደዚህ ነይ፡” አላት። ልብ በሉ፡ እዚህ ያረጋግጠዋል። ከየትኛው ምንጭ እንደነበረች እዚህ ያሳያል። “ሂጂና ባልሽን ይዘሽ ወደዚህ ነይ፡” አላት።

“ምንም ባል የለኝም፡” አለችው።

173 “እውነቱን ተናግረሻል፡” አላት። እዩት፡ ከጠየቃት ነገር ጋር የሚጋጭ ይመስላል፡ እና “ሂጂና ባልሽን ይዘሽ ነይ፡” አላት።

“ባል የለኝም፡” አለችው።

174 “እውነቱን ተናግረሻል፡” አላት። “አምስት ባሎች ነበሩሽና፡ አሁንም ከአንቺ ጋር የሚኖረው ባልሽ አይደለም፡” አላት።

175 ሴቲቱን ተመልከቷት፡ በዘመኑ ከነበሩ ካህናት ትለያለች! የዚያን ዘመን ካህናት ያንኑ ነገር አይተው፡ “ከሰይጣን ነው፣ ቴሌፓቲ ነው፣ ወይም—ወይም ብዔልዜቡብ ነው፡” ብለውታል። እያችሁ፡ ቃል ራሱ ያንን ተሰፋ መሰጠቱ ማየት አልቻሉም።

176 ነገር ግን ምስኪኗ ሴት ከማንኛቸውም ካህናቶች ይልቅ በቅዱስ ቃላት ተሻለች። እሷም አለች፡- “ጌታ ሆይ፣ ነቢይ እንደሆንክ አያለሁ። ከሚልክያስ ዘመን በኋላ፡ ለአራት መቶ ዓመታት አንድም ነብይ አልነበረንም። ግን፡”

አለችው፡ “የሚመጣ አንድ እንዳለ እናውቃለን፡ እርሱም መሲሕ ነው፡ እየጠበቅነው እንገኛለን። እርሱም ሲመጣ የሚያደርገው፡ እንደዚሁ ይሆናል።”

ኢየሱስም “እኔ እሱ ነኝ፡” አላት። ኣሜን።

177 ከምንጩ ውኃ ተሞልታ፡ እንሰራዋን በያዕቆብ ጉድጓድ አጠገብ ትታ፡ ወደ ከተማው እንደሮጠች አስተውላችኋል! እሱ የህይወት ምንጭ ነበር፡ ፍፁም ሲረጋገጥ አይታለች። እሷን ላስተዋውቃችሁ። የሕይወት ቃል መሆኑ ሲረጋገጥ፡ ሄደች። በምድረ በዳ የተመታው ያው አለት፡ ህያው ሆኖ መገኘቱ ስላረጋገጠች፡ ትታው ሄደች።

178 እኔም እላችኋለሁ፡ ያ ብዙ የምንናገርለት፡ በጥንት ዘመን የነበረው አምላክ፡ አሁን እዚሁ አለ፤ በጥቂት የሰነ መለኮት መረዳት ሳይሆን፡ በዚህ በመጨረሻው ቀን መንፈስ ቅዱስን በቤተክርስቲያኑ ላይ እንደሚያፈስ፡ ስለ ማረጋገጫው ባለኝ የግል እውቀት ነው። “የነበርኩ ነኝ” አይደለም። አሁንም ዘወትር በአሁናዊ አሰራሩ፡ “እኔ ነኝ፡” ነው።

179 ከዚያም ጉድጓዱ ጣዕሙን አጣ። በመንፈስ ቅዱሰ ጥምቀት፡ ወደ እግዚአብሔር ኃይል የሚገባ ሰው ሁሉ እንዲሁ ነው፡ የሐይማኖት ተቋማትን ጣዕም ያጣባቸዋል። ከእንግዲህ በተበረዘ ውኃ ውስጥ ያሉትን እንቁራሪቶች፡ እና እንሽላሊቶች፡ እና ነፍሳት፡ ወዘተረፈ አትመኙ። በነፍሳችሁ ውስጥ ዘወትር ፍሬሽ እና ንጹህ ከሆነው ምንጭ፡ ከእግዚአብሔር ቃል እየጠጣችሁ ነውና። አሁንም እንዲሁ ነው፡ የቃሉ እውነትነት ሲረጋገጥ ቀምሳችሁ ትክክል አለመሆኑን መርምሩ።

180 የውኃ ጉድጓድ ቢያገለግልም፡ ጊዜውን በጥሩ ሁኔታ አገልግሏል፡ አሁን ግን፡ እያችሁ፡ የህይወት ምንጭ ተገኝቷል፡ የያዕቆብ ጉድጓድ፡ ለመንፈሳዊ መጠጥ አይሆንም። ለምን፡ እነሱ ያሰቡት ነገር፡ ከዚያ ምንጭ ቢጠጡም፡ ምንም ችግር የለውም ነበር፡ አሁን ግን የሕይወት ምንጭ ራሱ በዚያ ተቀምጦ ነበር።

181 አሁን እኛ ያሉን ሰርዓቶች እና ድርጅቶች አያስፈልጉንም። በመጨረሻው ዘመን ላይ ነንና። እግዚአብሔርም በዚህ የፍጻሜ ዘመን የሚያደርጋቸውን ነገሮች ቃል ገብቷል። ቃሉም፡ ሲፈጸም አይተናል። የውትድርና ኃያላን፡ ተነስተው፡ ሲንቀጠቀጡ፡ እና “የሆነ ነገር ለመሆን ዝግጅት ላይ ነው፡” ብለው ሲያወሩ፡ ሰምተናቸዋል። የሆነ ነገር እንደሚሆን መንፈስ ቅዱስ እያሰጠነቀቀን እንዳለ ይሰማናል። ሁሉንም ነገር በቅደም ተከተል ተቀምጧል። ከሰርዓት ውጡ ወደ ፏፏቴው ቅረቡ። የሰ፡ ሰር።

182 ዓላማውን አገልግሏል፡ አሁን ግን ከምንጩ ጋር ፊት ለፊት ተገናኝታለች።

183 በዮሐንስ 7:37-38፣ ኢየሱስ በድንኳኑ በዓል በመጨረሻው ቀን (ምን አለ? )፡ ብዙ ሰነመለኮታውያን ባሉበት መኃል! “ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ።” “ማንም የተጠማ ቢኖር፡ ወደ እኔ ይምጣና፡ ይጠጣ። ቅዱሳን መጻሕፍት የሕይወት ውኃ ወንዝ ከውስጡ ይፈልቃል ብሎአልና።”

184 ሕያው ምንጭ ይህ ነው። ዛሬ ህዝቡ ጥሎት የሄደው ፏፏቴ ይህ ነው። ስለ ሐይማይኖት ሰርዓት፡ የሕይወትን ምንጭ ትተዋል። እሱን ላስተዋውቃችሁ። እሱ፡ ለኔ... አሁን እያጠቃለልኩ ነው።

185 እሱ፡ ለእኔ፡ አጋር፡ እና ልጁ በምድረ በዳ በሞት አፋፍ ሳሉ፡ ሕይወታቸውን ያዳነ ምንጭ ነው።

186 በኢሳይያስ ምዕራፍ 32 ላይ፡ ያለው ዓለት እርሱ እንደሆነ አምናለሁ፡ እርሱ በጥም ምድር ያ ዓለት ነው። ከዐውሎ ነፋስም እንደመጠጊያ ነው።

187 ዘካርያስ 13 ላይ፡ እርሱ በዳዊት ቤት ስለ ኃጢአታቸው፡ የተከፈተ ምንጭ ነው። እንደሱ እንደሆነ እምነዋለሁ። እናንተስ?

188 በመዝሙር 36:9 ላይ፡ እርሱ የዳዊት የሕይወት ምንጭ ነው። እርሱ የዳዊት የዕረፍት ውኃና፡ የለመለመ መስክ ነው። እርሱ ለዳዊት በወንዝ ዳር ያለውን ፈፋ ነው።

189 በዘፍጥረት 17፣ እሱ ለአብርሃም የሚያጠባው ጡት፡ ኤልሻዳይ ነው። ህይወቱ ባለቀች ጊዜ ግን፡ አሁንም… እግዚአብሔር ተናገረው።

190 “በመቶ ዓመት ሰው ላይ፡ እንዴት ይሆናል? እኔ አርጅቻለሁ፡ ሚስቴ አርጅታለች፡ እነዚህ ነገሮች እንዴት ሊሆኑ ይችላሉ? ”

191 እሱ ግን “እኔ ኤልሻዳይ ነኝ፡” አለው። **ኤል** ማለት፡ “የ” ማለት ነው፡ እና—እና **ሻዳይ** ማለት “ጡት፡” ሻዳይ ብዙ ቁጥር ነው፡ ይህ ማለትም “እኔ የማጠባ አምላክ ነኝ።”

192 የተነጫነጨ እና የታመመ፡ አቅሙ ሁሉ የከዳው ህጻን ልጅ፡ በእናቱ እቅፍ ውስጥ ገብቶ አቅሙን እንደሚመልስ ነው። በእርግጠኝነት። ይህ ብቻ አይደለም… መጥባት ሲጀምር፡ መነጫነጭ ያቆማል። በእናቱ ጡት፡ ጥንካሬውን በሚያገኝበት ጊዜ ይረካል።

193 የእግዚአብሔርንም የተሰፋ ቃል በልቡ የሚቀበል ሰው ሁሉም፡ “የተሰፋው ቃል ለእናንተና፡ ለልጆቻችሁ፡ ጌታ አምላካችን ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ፡” ነውና፡ እናንተም በዚያ ውስጥ እራሳችሁን ጣሉና አቅማችሁን መልሱ። ነጭናጫ ልጅ ሆይ፡ እመን! ለሚያምኑ ነውና።

194 ለአማኙ ግጥም፡ ገጣሚዎቹ ያገኟቸውን ብዙ መዝሙሮች አስባለሁ። ከመካከላቸው አንዱ አንድ ጊዜ፡ እንዲህ አለ፤

ከአማኑኤል ደም ስር የተቀዳ፡
የደም ምንጭ አለ፡
ኃጢአተኞች ከጅረቱ በታች ሲወድቁ
የኩነኔ እድፈት ሁሉ ያጥብላቸዋል።

የሚሞተው ሌባ የዘመኑ ምንጭ አየ
በሞት አፋፍ ሆኖ ተደሰተ፡
እኔም እንደ እሱ፡ አመጸኛ ነኝና
ኃጢአቴን ሁሉ እጠበኝ።

በእምነት ያንን ጅረት ካየሁ ጀምሮ
ከሚያፈሱ ቁስሎች የሚወርድ፡
የመቤዠት ፍቅር መዝሙሬ ሆኗል
እስክሞት ድረስም ይሆናል።

195 ለኔ፡ ከቃሉ ጋር ከሚቃረን ነገር ሁሉ የሚለያችሁ፡ የመለየት ውኃ ቃል እርሱ ነው። እኔ የምንጭ ውኃ እርሱ እንደሆነ የማምነው እርሱን ነው። የሰ፡ ሰር። ሰው-ሠራሽ ከሆኑ ከውኃ ጉድጓዶች፡ ወደ ሕያው ምንጭ የለየኝ ውኃ፡ ያ ነው። ወዳጄ፡ ሆይ፡ እርሱ ለእኛ በሆናቸው ነገሮች ላይ—እንዲሁ ዝም ብዬ... እንዲሁ መቀጠል ትችላላችሁ! አልፋና፡ ኦሜጋ ነው። መጀመሪያ፡ መጨረሻም ነው። የነበረውም፡ ያለውም፡ የሚመጣውም እርሱ ነው። እርሱ የዳዊት ሥርና ዘር ነው። የንጋት ኮከብ ነው። ለእኔ ሁሉ በሁሉ ነው።

196 ወንድም፡ እና፡ እህት ሆይ፡ ይሄን ካላገኛችሁት—ዐ... ድሜአችሁ በሙሉ፡ ሰው-ሰራሽ ከሆነው ትንሽ ጉድጓድ እየጠጣችሁ የኖራችሁ ከሆናችሁ፡ ዛሬ ጠዋት ያንን ጉድጓድ ትታችሁ ወደዚህ ምንጭ ለምን አትመጡም?

197 ለአፍታ ራሳችንን ዝቅ እናድርግ። ራሶቻችሁ ዝቅ እንዳሉ... [አንዲት እህት በሌላ ልሳን መዘመር ጀመረች። በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] ... እንደኔ እንደኔ፡ የመሰውያው ጥሪ። እስቲ ስንት ሰዎች አላችሁ?

198 ብ—ብዙ ጊዜአችሁን ስለወሰድኩባችሁ፡ መልእክቴን ከፋፍዬ እንድቆርጥ አድርጎኛል፡ ደ—ደንገጥ ብዬ ነበርና። መንፈስ ቅዱስ ግን የምለውን እንድታገኙ እንደሚፈልግ አምናለሁ። ሰሙኝ፡ በዚህ ዘመን ከእግዚአብሔር ጋር ትክክል ከመሆን የበለጠ አስፈላጊ ነገር የለም፤ እያችሁ፡ እራቶቻችን፡ ምንም ቢሆኑ፡ ምን። ጌታ እዚህ አለ። እንግዲህ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ፡ ያንን በህይወቴ አንድ ጊዜ ብቻ ሰምቻለሁ።

199 አሁንም... እዚህ የተገኛችሁ ሁላችሁ፡ "ሰንቶቻችሁ፡" አልልም። ከዚህ መጠጣት የምትፈልጉ ሁላችሁ፡ ለአፍታ ያህል፡ ለጸሎት በእግሮቻችሁ ቁሙ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ጌታ ይባርካችሁ።

200 እስቲ ሰንቶቻችሁ፡ አሁን እዚህ—ቆማችሁ ያላችሁ፡ እጃችሁን ወደ ላይ **እንዲህ** አንሰታችሁ፡ "እግዚአብሔር ሆይ፣ ሙላኝ፡ በእኔ ላይ ተመላለስ፡ ከዚህ ምንጭ ልጠጣ። ትክክል የሆነውን ነገር አላደረግኩምና፡ ለዚህም አንተ—ይቅር በለኝ። ሐጢአቶቼን እንድታጥብልኝ እፈልግሃለሁ። እኔም ከ—ከ—ከ፡ ከዛሬ ቀን ጀምሬ፡ እንደው... "? እንደው እየኝ! ማይ!

ከአማኑኤል ደም ሰር የተቀዳ፡
የደም ምንጭ አለ፡
ኃጢአተኞች ከጅረቱ በታች ሲወድቁ፡
የኩነኔአቸው እድፈት ይለቃል።
የኩነኔአቸው እድፈት ይለቃል፡
የኩነኔአቸው እድፈት ይለቃል፤
ኃጢአተኞች ከጅረቱ በታች ሲወድቁ፡
የኩነኔአቸው እድፈት ይለቃል።

201 አሁን፡ አንተ ክርሰቲያን አማኝ፡ ክርሰቶሰን እንደ ግል አዳኝህ የተቀበልህ፡ ገና እስከ አሁን ድረሰ... ከሌለህ፡ ምንጩ ያ ነው። እኔ የማውቀው የአምኑኤል የደም ሰሩ ምንጭ ብቻ ነው። እንግዲህ፡ እዚህ የተገኛችሁ ብዙዎቻችሁ...

202 ልክ በቀደም ማታ ከዶሮዎች ጋር በጓሮው ውሰጥ እንደሚራመድ ንሰር ብዬ እንደነገርኳችሁ ዓይነት ነው። ከዶሮዎች በሰተቀር ሌላ ምንም አያውቅም ነበር፡ ይሁን እንጂ ከዶሮዎቹ የሚለይበት የሆነ ነገር እንዳለው ያውቃል። በኋላ

እናቱ እሱን ለማደን መጣችና፡ ከላይ ጮኸች። የንሰር ጥሪ ነበር። እያችሁ፡ ከመጀመርያው ጀምሮ፡ ንሰር ባይሆን ኖሮ፡ ያንን ጥሪ መረዳት አይችልም ነበር። እያችሁ፡ እሱ...

203 የሆነ ነገር፡ የበቀለ ነገር ባይኖረው ኖሮ፡ በጭራሽ ህይወትን አያፈራም ነበር። ዘር የሆነው፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ በእናንተ ውስጥ ካለ፡ ወደ ህያው ማንነት ሊያበቅለው የሚችል መንፈስ ቅዱስ አሁን በዚህ ሰፍራ አለ።

204 እዚህ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ያልተሞላችሁ ስንት ሰዎች አላችሁ፡ እባካችሁ እጆቻችሁን ወደላይ ታነሳላችሁን? በየአቅጣጫው፡ በሁሉም ቦታ፡ በእውነት እና በሐቀኝነት፡ መንፈስ ቅዱስን ካልተቀበላችሁ፡ እና መቀበል ከፈለጋችሁ፡ እጃችሁን አንሡ። የትም ብትሆኑ፡ ለአፍታ ብቻ፡ እጃችሁን ወደ ላይ አንሡ።

205 አሁን የምፈልገው፡ እንደቆማችሁ ዙርያችሁን ተመልከቱ፡ እጃችሁን አንድ ሰው ላይ እንድትጭኑበት እፈልጋለሁ።

206 መንፈስ ቅዱስ የምትፈልጉትን ሁላችሁን እንደሚሞላችሁ አምናለሁ። አሁን በካፊቴሪያው ውስጥ ስላለው ምግብ አታስቡ፡ እዚህ ስላለው ምግብ እናስብ። ዋናው ይህ ነው። ህይወት ይህ ነው። እያችሁ፡ ህይወት ይህ ነው።

207 አሁን እያንዳንዳችሁ ወደ ቀኛችሁ ዘወር ብላችሁ እጆቻችሁን እርስ በርሳችሁ ላይ ጣሉ። "እጃቸውንም ጫኑባቸው!" እጃችሁ ስላረፈበት ሰው እንድትጸልዩ እፈልጋለሁ...

208 አሁን ስለመውጣት አታስቡ፡ ስለ ሌላ ነገር አታስቡ። እስቲ አስቡት፡ አሁን፡ መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዱን ሰው ለመሙላት መጥቷል። ልባችሁን ክፈቱና፡ የጉድጓዱን ውኃ ሁሉ አውጥታችሁ፡ እንዲህ በሉ፦ "የሕይወት ምንጭ ሆይ፡ ወደ እኔ ግባ። አቤቱ አምላክ ሆይ፡ በቸርነትህና በምሕረትህ፡ ሙላኝ።"

209 ጌታ ኢየሱስ፡ የማያልቅ ምንጭ ሆይ! እግዚአብሔር ሆይ፡ እያንዳንዳቸውን እንድትሞላ፡ እጸልያለሁ። መንፈስ ቅዱስ ይውረድ። እግዚአብሔር ሆይ፡ ስለ ሌላ ነገር ሁሉ እንድንረሳ እጸልያለሁ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ አሁን፡ በመካከላችን ይውረድ፡ በሁሉም ሰፍራዎች የህይወትን ውኃ፡ በነጻ፡ ይሰጠን። እግዚአብሔር ሆይ፡ ይህን ስጥ። ጌታ ሆይ፡ የጸሎቱ፡ እና የዝማሬው ፍሰት፡ በህብረት በሚወርድበት ጊዜ፡ መለኮታዊ ህልውናህን፡ መገኘትህን እያወቅን፡ ወደ ምንጩ መቅረብ እንፈልጋለን። እውነተኛውን፡ እና ትክክለኛውን የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት እንጠማለን። ጌታ ሆይ፡ የነዚህ ሰዎች ልመና እርሱ ነውና። በዚህ በትክክለኛው ጊዜ፡ በእግዚአብሔር ቸርነት እንዲሞሉ፡ እጸልያለሁ። እግዚአብሔር ሆይ፡ አቤቱ ሰጠን። የልጆችህን ጸሎት ሰማ። በሰውነታቸው ላይ ውረድ፡ የእግዚአብሔር ኃይል፡ እና መንፈስ ቅዱስ፡ በላያቸው ላይ ይረፍ። አምላክ ሆይ፡ አቤቱ አድርግልን።

210 በመካከላችን ስለቆመው የኃያሉ የሰማይ አምላክ መገኘት፡ ስለ መታደስ፡ እናመሰግንሃለን። ጌታ ሆይ፡ በዚህ የቀትር በኋላ ላይ፡ መግበን! ጌታ ሆይ ከገበታህ ምግብ እንፈልጋለን። ጌታ ሆይ፡ አሁን፡ መግበን። በሕይወታችን፣ በመንፈስ ቅዱስ መግበን። የተራበችና የደረቀች ነፍሳችን ተጠምታለች። በመዝሙሩ ትርጓሜ እንዳልከው፡ "በደረቅ መሬት ላይ ውኃ ታፈሳለህና።" ይሁን፡ ጌታ ሆይ። ቃልህ በልጆችህ ልብ ይገለጥ፡ "በደረቁ መሬቶች ላይ፡

ውኖች ይሁኑ። የዘላለም አምላክ ሆይ፡ የባሪያህን ጸሎት ስማ፡ በረከትንንም ሰጠን። ኣሜን።

አቤት፡ ኢየሱስን ሰወደው፡

211 አሁን እሱን ብቻ አመሰግኑት። መንፈስ ቅዱስ እዚህ ነው፡ እወቁ። ካልተቀበላችሁት፡ የራሳችሁ ጥፋት ነው።

... ኢየሱስን ሰወደው፡

"ከእነዚህ አብልጠህ ትወደኛለህን?"

... ኢየሱስን ሰወደው፡
እሱ መጀመሪያ ስለወደደኝ ነው።

አቤት፡ ሰወደው... (እግዚአብሔር ይመስገን!)
አቤት፡ ሰወደው... (በዚህ ሰአት ቢመጣስ?)
አቤት፡ ኢየሱስን ሰወደው፡
እሱ መጀመሪያ ስለወደደኝ ነው።

እርሱን ፈጽሞ አልተወውም፡
እርሱን ፈጽሞ አልተወውም፡
እርሱን ፈጽሞ አልተወውም
እሱ መጀመሪያ ስለወደደኝ ነው።

ድንቅ ነው፡ ድንቅ ነው፡ ኢየሱስ ለእኔ፡
መካሪ፡ የሰላም አለቃ፡ ኃያል አምላክ ለኔ፤
አቤት፡ ያዳነኝ፡ የጠበቀኝ ከኃጢአት ከእፍረት
ታዳጊዬ ድንቅ ነው፡ ሰሙ ይመስገን...

212 አሁን ለእርሱ እንዘምርለት!

ድንቅ ነው፡ ድንቅ ነው፡ ኢየሱስ ለእኔ፡
መካሪ፡ የሰላም አለቃ፡ ኃያል አምላክ ለኔ፡
አቤት፡ ያዳነኝ፡ የጠበቀኝ ከኃጢአት ከእፍረት
ታዳጊዬ ድንቅ ነው፡ ሰሙ ይመስገን!

213 ያንን የሚሰማችሁ ሁሉ "ኣሜን፡" በሉ። [ጉባኤውም "ኣሜን፡" አለ።—አርታዒ።] ኦህ፡ ሃሌሉያ! አሁን አንዳንድ ሰዎች፡ በመንፈችስ ቅዱስ ሲመጡ እያለሁ።

የጠፋሁ ነበርኩ፡ አሁን ተገኘሁ፡ ከኩነኔ ነጻ ነኝ፡
ኢየሱስ ይሰጣል ነፃነት እና ሙሉ ደህንነት፡
ያዳነኝ፡ የጠበቀኝ ከኃጢአትና ከእፍረት
ታዳጊዬ ድንቅ ነው፡ ሰሙ ይመስገን...

አሁን እጃችንን አንስተን ከልባችን እንጸልይ-...

ኦ፡ ድንቅ ነው፡ ድንቅ ነው፡ ኢየሱስ ለኔ፡
መካሪ፡ የሰላም አለቃ፡ ኃያል አምላክ ለኔ፡
አቤት፡ ያዳነኝ፡ የጠበቀኝ ከኃጢአትና ከእፍረት፡
ታዳጊዬ ድንቅ ነው፡ ሰሙ ይመስገን!

214 ትወዱታላችሁን? ኦህ፡ ድንቅ ነው! በእርሱ ነጻ ሆነው፡ ኃጢአተኞች ከሰው ፍርሃት፡ ከኩነኔ ሁሉ የሚላቀቁበት፡ በደም የተሞላው ምንጭ የተመሰገነ ይሁን። ሃሌ ሉያ! ኦህ፡ ማይ፡ በእውነት ድንቅ ነው!

215 አሁንም ያንን እንደገና እየዘመርን፡ የሜቶዲስት፡ የባፕቲስት፡ የካቶሊክ፡ የፕሬስባይቴሪያን ሁላችሁም፡ "ኢየሱስ ለእኔ፡ ድንቅ ነው፡" ብለን፡ እየዘመርን ባለንበት፡ አጠገባችሁ ወዳለው እየዞራችሁ ሁላችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ፡ ጥሩ የድሮ-አንድነት ፍጠሩት። እኔ የምወደው ያ ነው፡ ታውቃላችሁ። አሁን፡ ሰላም እየተባባልን፡ ኑና እንዘምረው።

ኦ፡ ድንቅ ነው፡ ድንቅ ነው፡ ኢየሱስ ለኔ፡

216 [ወንድም ዴሞስ ሻካሪያን ከወንድም ብራንሃም ጋር ተነጋገረ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ስለ ፕሬዘዳንት ጆንሰን አሁን ሰማሁ፡ በልብ ሕመም ወደ ሆስፒታል በፍጥነት ተወስዷል፡ እና ምናልባት ስለ እርሱ እና ስለ ሀገራችን መጸለይ አለብን።" አንድ ሰውም "ትንሽ ቆይ፡" አለ።—እርታዒ።]

... ድንቅ ነው፡ ኢየሱስ፡ (በትክክል።)
ኦህ፡ መካሪ፡ የሰላም አለቃ፡

217 [ወንድም ሻካሪያን እንደገና ወንድም ብራንሃምን አነጋገረው፡ "ምን አልከኝ፡ ምን አልከኝ፡ ለአንድ ደቂቃ መውጣት ትፈልጋለህ? " ወንድም ኧርል ፕሪኬት በግሩም መዝሙር **ድንቅ ነው፡** ጉባኤውን እየመራ ነው። በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ። ጉባኤ **የህይወት ወንዝ አለ** እያለ ይዘምራል። በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—እርታዒ።]

መጽሐፍ ቅዱስ "ለባለ ሥልጣኖች ጸልዩ፡" ይላል።

218 የሰማይ አባታችን ሆይ፡ ለሀገራችን መሪ፡ ለፕሬዝዳንታችን በፍጹም መጓጓት ቆመናል። ጌታ ሆይ፡ ይህን በፍፁም ላያውቀው ይችላል፡ አንተ ግን ታውቃለህ። ወንድም ጆንሰን፡ በአንተ እንደሚያምን ተናግሯልና እጸልያለሁ። እና፡ አባት ሆይ፡ በልብ ድካም እንደተጠቃ፡ ተረድተናል። አምላክ ሆይ፡ እጸልያለሁ፡ ህይወቱን አትርፋት። እንደው፡ በአሁን ሰአት—አገራዊ ቀውስ ውስጥ ነን። ጌታ ሆይ፡ መንፈስህ በእርሱ ላይ ይውረድ። እና አሁን፡ በሆስፒታልም ይሁን ወይም የትም ቢሆን፡ መንፈስህ ወደዚያ ዋልተር ሪድ ሆስፒታል ይውረድ እና ህይወቱን ለማትረፍ፡ ሰውነቱን ይዳሰሰ። ጌታ ሆይ፡ ሰውዬው ጫና ውስጥ ነው፡ ከምንረዳው በላይ ጫና አለበት። ስለዚህ፡ እግዚአብሔር ሆይ፡ እንደ አማኞች እና እንደ ሕዝብ አካል፡ ስለ መሪያችን እንጸልያለን፡ በዚህ በታላቁ ወቅት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እድሜውን እንድታረዝምለት ነው። ኣሜን።

**የተቀደዱ የውኃ ጉድጓዶች** AMH65-0123

(Broken Cisterns)

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በእንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ ቅዳሜ ጥዋት፡ ጥር 23፡ 1965 U.S.A. ፎኒክሰ፡ አሪዞና፡ በራማዳ ኢን፡ ለፋል ጎሰፔል ቢዝነሰ ሜን ፌሎሺፕ ዓለም አቀፍ የቁርሰ ሰነ ሰርዓት ላይ ተላልፎ፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ እንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይሰ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግሰ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2023 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈለጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡



Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org